# ድሬ

19ኛ ዓመት | ቁጥር 859 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ | ጥር / 01 / 2016 ዓ.ም


## በአራቱ ክላስተሮች የተሰሩ ፕሮጀክቶች ተመረቁ



በድሬዳዋ አስተዳደር በአራት ክላስተር የገጠር ወረዳዎች የተገነቡ የመስኖ ግድቦች፣የንጹሁ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች እንዲሁም ሌሎች መሰረተ ልማቶች ተመረቁ፡፡

የአስተዳደሩን የመልማት እድልን የመወሰን እምቅ አቅም መኖሩን ማሳያ የሆነው የግብርና ዘርፍ ስራ ውጤት ሰሞኑን የድሬደዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሀር እና የካቢኔ አባላት የምርቃት መርሀግብር እና የስራ ምልከታ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በምርቃቱ ማጠቃለያ መርሀ ግብር ላይም የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሀር ሲገልጹ አስተዳደሩ ዝናብ አጠር ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የተሰሩ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

እነዚህን አመርቂ የግብርና ስኬቶች በማስፋት የምንፈልጋትን የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር የአርሶ አደሩን ችግሮች በመመልከት ያሉትን ማነቆዎች የማጥራት ስራ እንደሚሰራም ነው የገለጹት፡፡

የአስተዳደሩ የግብርና ውሃ ማዕድን እና ኢነርጂ ቢሮ ሀላፊ አቶ ኑረዲን አብደላ እንደተናገሩት አስተዳደሩ የመስኖ መሰረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት የአርሶ አደሩን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

## የተቋማት የ2016 በጀት አመት የሁለተኛው ሩብ አመት የመልካም አስተዳደር እቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ ተካሄደ



የድሬዳዋ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በአስተዳደሩ የሚገኙ ተቋማትን የ2016 በጀት አመት የሁለተኛው ሩብ አመት የመልካም አስተዳደር እቅድ አፈፃፀምን የሴክተር ተቋማት የለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክተሮች እና የወረዳዎች የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ማስተባበሪያ ኃላፊዎች በተገኙበት ገምግሟል።

በመድረኩ የተመረጡ 3 ተቋማት የሩብ አመት አፈፃፀማቸውን ካቀረቡ በኋላ ቢሮው በተቋማቱ ሪፖርት ከተደረገለት አፈፃፀም ባሻገር በየተቋማቱ የተደረገን ክትትልና ድጋፍ መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ የአፈፃፀም ግብረ መልስ ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል።

በመድረኩ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የድሬዳዋ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሰቦ አህመድ እንደገለፁት የመድረኩ ዋንኛ አላማ ተቋማቱ ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች አንፃር በየጊዜው የሚነሱባቸውን የውስጥ እና የውጭ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመለየት፣ በማቀድ እና በመፍታት ረገድ በሩብ አመቱ ያስመዘገቡትን አፈፃፀም በጋራ ለመገምገም እና የቀጣይ አቅጣጫ ለማስቀመጥ መሆኑን ገልፀው፤ ከዚህም አንፃር በየተቋማቱ ከሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ብዛት ጋር ሲነፃፀር በርካታ ስራዎች መሰራት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ በተለይም በየተቋማቱ የተመደቡ የዘርፍ አመራሮች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡም መልዕክት አስተላልፈዋል።

በድሬዳዋ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ጥናት፣ ክትትል እና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ግርማ ዘለቀ በበኩላቸው በአስተዳደር ደረጃ ከህዝብ በተደጋጋሚ ከሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መካከል ከመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የሚገኛኙ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙ መሆኑን ገልፀው፤

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

## የገናን በዓል ስናከበር ለአተት በሽታ የምንጋለጥበትን ሁኔታ በመከላከል ሊሆን እንደሚገባ ተገለፀ




ለክርስትና እምነት ተከታዮች የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ያስተላለፉት የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ጽጌሬዳ ክፍሌ በበዓሉ ዝግጅትና አከባበር ወቅት ሊደረጉ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች በቢሯቸው መግለጫ ሰጥተዋል ፡፡

የገናን በዓል ስናከብር ለአጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት( አተት) በሽታ የምንጋለጥበትን ሁኔታ መቀነስ በምንችልበት መልኩ ሊሆን እንደሚገባ ያስገነዘቡት ኃላፊዋ ከአመጋገባችን ጀምሮ ማድረግ ስለሚገቡ ጥንቃቄዎች የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ በቅርብ ጊዜ በአስተዳደራችን ብሎም በአጎራባች ክልሎች የተከሰተውን የአጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት በሽታን በመከላከል ለበአሉ የሚከናወኑት የእንሰሳት እርዶች በአግባቡ መሆን እንዳለበትና፤ የምንመገባቸው ምግቦችም ንፅህናቸው በጠበቁ መልኩ ማዘጋጀት እንደሚገባ አሳስበዋል።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# በድሬዳዋ አስተዳደር ባሉ የገጠር ወረዳዎች የተሰሩ የልማት ፕሮጀክቶች ተመርቀው ለአገልግሎት ክፍት ሆኑ

በአስተዳደሩ የገጠር ወረዳዎች ውስጥ አንዱ በሆነው የጀልዴሳ ወረዳ በጭሪሚቲ፣ ደበሌ፣ በለገዲኒ እና በአያሌ ቀበሌዎች የተገነቡ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ተመረቁ።

የድሬደዋ አስተዳደር ክቡር ከንቲባ ከድር ጁሃር እና ምክትል ከንቲባ ክቡር ሀርቢ ቡህ እንዲሁም የካቢኔ አባላትን ያካተተው ቡድን በገጠር በጀልዴሳ ወረዳ ተገንብተው የተጠናቀቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን መርቀዋል።

በድሬዳዋ አስተዳደር በግብርና እና ውሀ ማእድን ኢነርጂ ቢሮ የመስኖ መሰረተ ልማት የፕሮጀክቶች የምርቃት መርሀ ግብር ባሳለፍነው ሳምንት በአስተዳደሩ በጀልዴሳ ወረዳ አስተዳደር የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታቸው ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆነዋል።

ከተመረቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችም መካከል የጭሪሚቲ የመስኖ ውሃ ልማት ፣የጀልዴሳ ሼክዌይስ የመስኖ ልማት፣የደበሌ አነስተኛ መስኖ ልማት ለገዲኒ ግድብ፣አያሌ መልቲ ቪሌጅ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት እንዲሁም የሞባይል ኔትዎርክ ታወር ፕሮጀክቶች ይገኙበታል።

ሼክዌይስ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት 120 ሄክታር መሬት ሊያለማ የሚችል ሲሆን የመስኖ ልማቱ በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ ሲገባ 33,600 ኩንታል የአትክልት ምርት እንደሚገኝ ይጠበቃል።

የጭሪሚቲ አነስተኛ መስኖ ፕሮጀክት 10 ሄክታር መሬት ሊያለማ የሚችል ሲሆን የመስኖ ልማቱ በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ ሲገባ 2800 ኩንታል የአትክልት ምርት ማምረት ያስችላል ተብሏል።

በተያያዘ ዜናም በድሬዳዋ አስተዳደር በገጠር በአሰሊሶ እና በዋሂል ወረዳ አስተዳደሮች የተገነቡ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ተመርቀዋል።

አስተዳደሩ የመስኖ መሰረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት የአርሶ አደሩን እና አርብቶ አደሩን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በትኩረት እየሰራ መሆኑ ተመልክቷል፡፡









በፕሮጀክቱ ምርቃት ላይም የአስተዳደሩ የግብርና ውሃ ማዕድን እና ኢነርጂ ቢሮ ሀላፊ አቶ ኑረዲን አብደላ እንደተናገሩት የፕሮጀክቱ ግንባታ በተለይም የዝናብ እጥረት በስፋት የሚታይባቸውን ወረዳዎች መሰረት በማድረግ መከናወኑ ጥቅሙን የጎላ እንደሚያደርገው ገልፀዋል።

በአሰሊሶ ወረዳ አስተዳደር ተጠናቆ ለአገልግሎት የበቃው የመስኖ ፕሮጀክት 162 ሄክታር መሬት ማልማት የሚችልና ከ423 የሚበልጡ አባወራዎችን ኑሮ በተጨባጭ ለመቀየር የሚያስችል ነው ብለዋል።

ከአሰሊሶ ወረዳ የሁላሁሉል ቀበሌ ነዋሪዎች እንደገለጹት የህብረተሰቡ የዘመናት ጥያቄ የነበረውን የመስኖ ልማት ተጠቃሚነት በመንግስት ምላሽ በመሰጠቱ አመስግነዋል፡፡

በአካባቢያቸው ተገንብቶ ለአገልግሎት የበቃው የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች አትክልትና ፍራፍሬ ከማልማት ባሻገር በተጓዳኝ በሌሎች ገበያ ተኮር የግብርና ስራዎች ላይም መነሳሳት እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል።

**በሰላም ለማ**

**ፎቶ:- ሙሉዓለም ደሴ እና ደረጀ ትሁነህ**

# የድሬዳዋ ነዋሪዎች የአስተዳደሩንም ሆነ የሀገርን ሰላም በዘለቄታዊነት ለማረጋገጥ ከምንግዜዉም በላይ የሰላም ባለቤት ሆነው እንደሚሰሩ ገለፁ

በድሬዳዋ በሰላም ጉዳይ ላይ የሚንቀሳቀሱ የህብረተሰብ ክፍሎችና የተለያዩ ተቋማት የተሳተፉበት ሰላምን የማጠናከርና የማስቀጠል አላማ ያነገበ ጉባኤ ተካሂዷል።

በአስተዳደሩ በተካሄደዉ የህዝብ ለህዝብ የሰላም ጉባኤ ላይ የተገኙት የድሬዳዋ አስተዳደር ፍትህ ፀጥታና የህግ ጉዳዮች ም/ቢሮ ኃላፊ አቶ አብደላ በከር የጉባኤው መዘጋጀት አሁን ላይ ያለዉን ሰላም ጠብቆ የበለጠ በቀጣይም አስተማማኝ አድርጎ ለማስቀጠል ብሎም በየደረጃው የሚገኘው የህብረተሰብ ክፍል ለሰላም እያበረከተ የሚገኘውን አስተዋጽኦ ለማጠናከር የሚረዳ ስለመሆኑ ገልፀዉ፤ እንደ ድሬዳዋ አስተዳደር በቀጣይም ለሰላም ቅድሚያ ሰጥቶ መስራት ከዚህ በተሻለ ተጠናክሮ ይቀጥላል ነዉ ያሉት።

በእዚሁ ጉባኤ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ የccrda ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ንጉሱ ለገሰ በበኩላቸዉ በመድረኩ ባስተላለፉት መልእክት በድሬዳዋ ያለዉ ሁለተናዊ ሰላም ለሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ምሳሌ ጭምር የሚሆን ስለመሆኑ ተናግረዉ፤ ለዚህም ለአስተዳደሩንና ለመላው ነዋሪ ህብረተሰብ ምስጋናቸዉን ያቀረቡ ሲሆን ድርጅታቸዉ ለዘላቂ ሰላም መረጋገጥና የህዝቦች አብሮነት በቀጣይ ድጋፍ የሚያድርግ ስለ መሆኑም ተናግረዋል፡፡





ሌላኛዉ በመድረኩ ተገኝተዉ መልእክት ያስተላለፉት የኒዮ ሶሳይቲ አለም አቀፍ ማህበር ም/ዳይሬክተር ዶ/ር አሰፋ ወዳጆ ማህበራቸዉ በመላ አለም የሚገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጲያዊያን የተቋቋመ ስለመሆኑ ገልፀዉ፤ ዘላቂ ሰላምን በማስፈን የህዝቦች አብሮነትና ወንድማማችነትን እንዲጠናከር በድሬደዋ የሰላም መአከል ከመገንባት ጀምሮ በተለያዩ አካባቢዎች ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ችግር ፈቺ የሆኑ የልማት ተግባራት በቀጣይ ግዜያት በማህበራቸዉ ተግባራዊ እንደሚደረጉ ይፋ አድርገዋል፡፡

በእዚሁ ሰላምን የማጠናከርና የማስቀጠል አላማ ባነገበዉ የሰላም ጉባኤ በድሬዳዋ ዩንቨርስቲ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ባከናወኑት ዶ/ር ሮባ የመወያያ ፅሁፍ ቀርቦ በተሳታፊዎች ዉይይት የተካሄደ ሲሆን የመድረኩ ተሳታፊዎችም በሰጡት አስተያየት ሰላምን መጠበቅና ማስቀጠል የዜጎች ኃላፊነት ጭምር እንደ መሆኑ የተካሄደው የሰላም ጉባኤ የበለጠ መነቃቃት የፈጠረ ስለመሆኑ ተናግረዉ፤ የድሬዳዋንም ሆነ የአገርን ሰላም ይበልጥ አስጠብቆና አጠናክሮ ለማስቀጠል የድርሻቸውን እንደሚወጡ ተናግረዋል።

የድሬዳዋ አስተዳደር ፍትህ ፀጥታና ህግ ጉዳዮች ቢሮ ከኒዮ ሶሳይቲ አለምአቀፍ ማህበር ጋር በመተባበር ባዘጋጀዉ የመሰረተ ሰላም ማኔፌስቶ የህዝብ ለህዝብ የሰላም ጉባዔ የኃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች ፤ ሴቶች፣ ወጣቶችና ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮችና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ሃላፊዎችና ተወካዮች ተገኝተዋል፡ ፡ ዘገባው የድሬዳዋ አስተዳደር ፍትህ ፀጥታ እና ህግ ጉዳዮች ቢሮ ህዝብ ግንኙነት ክፍል ነው፡፡

## ርዕሰ - አንቀጽ

# የተጠበቀው ባልተጠበቀው መንገድ የመጣበት...

የክርስቶስ የልደት በዓል ሁለት አስደናቂ ነገሮች የተፈጸሙበት ነው፡፡ የተጠበቀው ባልተጠበቀው መንገድ የመጣበት እና ያልተጠበቁት ባልተጠበቀ ቦታ የተገኙበት ነው፡፡ በኦሪትና በነቢያት ክርስቶስ ይመጣል የሚለውን ቃል የሰሙና ያነበቡ ብዙዎች ነበሩ፡፡ የጠበቁት ግን በነገሥታት ቤተ መንግሥትና በባለጸጎች እልፍኝ ውስጥ ነበር፡፡ የዓለምንና የሰው ልጅን ታሪክ የቀየረው ክርስቶስ በበረት ውስጥ ይወለዳል ብሎ የጠበቀ አልነበረም፡፡ በዚህም የተነሣ የዓለም ታሪክ በአስደናቂ ሁኔታ ሲቀየር ዓለም ራሷ ግን ተኝታ ነበር፡፡

የዓለምንና የሀገርን ታሪክ የሚቀይሩ ነገሮች በተለመዱና በሚጠበቁ መንገዶች ላይመጡ ይችላሉ፡፡ ብዙዎች በሚያውቁትና በሚተነትኑት አካሄድም ላይከሡቱ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ መረዳት የሚገኘው እኛ የማናውቀው፣ ያልደረስንበትና የማንገምተው ሌላም መንገድ ሊኖር እንደሚችል ለመቀበል ከተዘጋጀን ብቻ ነው፡፡ ነገሮች ሁሉ እኛ በምናውቀው፣ በምንገምተውና በለመድነው መንገድ ብቻ እንዲመጡ ከጠበቅን ሊያልፉን ይችላሉ፡፡ የቤተልሔም ከተማና የይሁዳ አውራጃ ሰዎች የዓለምን ታሪክ ከቀየረው ከክርስቶስ ልደት ሳይሳተፉ የቀሩት ከለመዱትና ከሚያውቁት ውጭ ለሚመጣ ነገር ዝግጁዎች ስላልነበሩ ነው፡፡

የቤተልሔም ከተማና የይሁዳ አውራጃ ሰዎች በለመዱትና በሚያውቁት መንገድ የሚመጣን ነገር ሲጠብቁ፣ ባልለመዱትና በማያውቁት መንገድ የሚመጣን መፍትሔ ለመቀበል ዝግጁ የሆኑ ሌሎች አካላት ቤተልሔም ደርሰው ነበር፡፡ እረኞችና ሰብአ ሰገል፡፡ ሌሊቱን ሙሉ መንጋቸውን ሲጠብቁ ያደሩት የቤተልሔም እረኞች በአካባቢያቸው የነበሩትን መላእክት ለመመልከት ዕድል አግኝተዋል፡፡ ጊዜው ምሽት ነው፡፡ ምሽት ደግሞ የዕንቅልፍ ጊዜ ነው፡፡ ለሕዝብ ቆጠራ ወደ ቤተልሔም የመጡ ሰዎች ከተማዋን አጨናንቀዋታል፡፡ ከዚህ ያለፈ እንግዳ ነገር የጠበቀ የቤተልሔም ሰው የለም፡፡ ሁሉም የተለመደን ነገር በተለመደ መንገድ በማከናወን ተኝቷል፡፡

እረኞቹ ግን ከተኛው ማኅበረሰብ ተለይተው በሜዳ ላይ በንቃት ነበሩ፡፡ ይሄ ብቻ አይደለም፡፡ የዓለምን ታሪክ የቀየረው ክርስቶስ በእንግዶች ማደሪያ ሥፍራ ስላላገኘ የመጣው ወደ በረት ነው፡፡ የከተማው ሰዎች ሊያደርጉ ያልደፈሩትን እረኞቹ በረታቸውን ለዮሴፍና ለድንግል ማርያም ለቅቀው ወደ ሜዳ ወጡ፡፡ እረኞቹ ከሕዝቡ የተለየ መንገድና የተለየ ዝግጁነት ነበራቸው፡፡ በዚህ የተነሣ ከሊቃውንቱ፣ ከፈሪሳውያኑና ከሰዱቃውያኑ ተለይተው ያልታሰበውን ታሪክ ያልታሰቡት እረኞች ለማየት በቁ፡፡

የቤተልሔምን ሰዎች ብቻ ሳይሆን ንጉሥ ሄሮድስንም ባስደነገጠ መንገድ ሰብአ ሰገል ከምሥራቅ ‹የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው› እያሉ ከእረኞቹ ቀጥለው መጡ። ማንም አልጠበቀም፡፡ ያልተጠበቁት ሰብአ ሰገል ባልተጠበቀ ቦታ በበረት ተገኙ፡፡ ካልተለመደ ሥፍራ፣ ባልተለመደ መንገድ ተጉዘው፣ ያልተጠበቀ ቦታ ተገኙና ያልጠበቁትን ተአምር አዩ፡፡

ሀገርን ምንጊዜም የሰው ልጅ ሲጓዝባቸው በኖሩ መንገዶች ብቻ መታደግ አይቻልም፡፡ ሰው ሁሉ በሚያውቃቸው፣ በለመዳቸውና በተረዳባቸው መፍትሔዎች ብቻ ሀገርን መመንጠቅ አይቻልም፡፡ መኪኖችና አውሮፕላኖች በሚጓዙበት መንገድ መንኮራኩሮችን ወደ ሕዋ መውሰድ እንደማይቻለው ሁሉ፡፡ ወደ ሕዋ ለመሄድ የምድር ስበትን ሰብሮ፣ በፍጥነትና በኃይል ባልተለመደ የጉዞ ስልት መመንጠቅን ይጠይቃል፡፡

እንዲህ ያለ ጉዞ ከተለመደውና ከሚታሰበው መንገድ ወጥቶ መሄድን የግድ ይላል፡፡ ስለዚህም ይሄንን መንገድ የሚረዳ ከሚጠበቀውና ከሚታሰበው ውጭ ለመጓዝ ፈቃደኛ የሆነ ወገንን ይፈልጋል፡፡ አሁን ሀገራችን ያለችው እንዲህ ባለ ጉዞ ላይ ነው፡፡

በተለመደ እሽክርክሪት ነባር ችግሮችን ፈትቶ አዲስ ውጤት ማስመዝገብ አይቻልም፡፡ የተለየ፣ ያልተጠበቀ፣ ከምናውቀው የወጣና ያልታሰበ መንገድ ይፈልጋል፡፡ በርግጥ እንዲህ ያለው መፍትሔ በተለመደው መንገድ ለሚያስቡና ለሚጓዙ እንግዳና የሚረብሽ እንደሚሆን እሙን ነው፡፡

ለመቀበልና ለማመንም ይከብዳቸዋል፡፡ እንደ እረኞች ዝግጁ እንደ ሰብአ ሰገል አሰላሳይ የሆኑ ወገኖች ግን ‹የት ነው?› እያሉ ፈልገው ይደርሱበታል፡፡ በተለመደው መንገድ የተለመደውን የሚከውኑ ወገኖች ቢገርማቸውም፤ ባልተለመደው መንገድ የሚመጣው እንግዳው መፍትሔ ግን፣ ታሪክን ላይመለስ መቀየሩ አይቀሬ ነገር ነው፡፡ መጀመሪያ የሚቀበሉት ጥቂቶች ቢሆኑም እየቆዩ ግን ብዙዎች እየተረዱትና እየተቀበሉት መሄዳቸው ርግጥ ነው፡፡

የክርስቶስን ልደት ስናከብር በልደቱ ካገኘነው በረከትና መዳን ቀጥለን ዓለም የተቀየረበትን መንገድ ማጤንና እኛም የምንሄድበትን መንገድ መገምገም አለብን፡፡ ሁሉም ነገር ለምክርና ለተግሣጽ እንዲሆነን ተጽፏልና፡፡

ይህ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ በእንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አደረሳችሁ መልዕክታታቸው የተናገሩት ነው፡፡

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

## አጀንዳ

# ፎረንሲክ ሳይንስ ምንድነው?

በዛሬው አጀንዳችን ስለ ፎረንሲክ ሳይንስ ምንነት እንዳስሳለን! ፎረንሲክ የሚለውን ቃል ብዙዎቻችን ሰምተነው እናውቃለን ብዬ ተስፋ አደርጋለው፡፡ ትክክለኛ ትርጓሜውን በተመለከተ ግን በብዙዎቻችን መረዳት ያለ አይመስልም፡፡ ለአንዳንዶች ፎረንሲክ ሳይንስ ሲባል የረቀቀና ጥቂት በሙያው የተካኑ ፖሊሶች ብቻ የሚረዱትና የሚጠቀሙበት ፖሊሳዊ ሳይንስ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የፎረንሲክ ሳይንቲስት ለመሆን ፖሊስ ወይም መርማሪ መሆን አይጠይቅም፡፡ እንዲያውም ሳይንሱ በእግሩ እንዲቆም ያደረጉት የዘርፉ ፈር-ቀዳጆች አብዛኛዎቹ በፖሊስነት ሞያ ውስጥ አላለፉም፡፡

ፎረንሲክ ሳይንስ በአጭር አነጋገር ሳይንሳዊ ዘዴ በመጠቀም ከህግ አፈጻጸም የሚመነጩ ጉዳዮችን ወይም ችግሮችን የሚፈታ ሳይንስ ማለት ነው፡፡ ሰፋ ባለ ትርጓሜው ለፍትሕ ስርዓት አገልግሎት የሚውል ማንኛውም ሳይንስ ሁሉ የፎረንሲክ ሳይንስ ነው፡፡

ከተፈጻሚነት አድማሱ አንጻር ሳይንሱ ለወንጀል ብቻ ሳይሆን ለፍትሐብሔር ጉዳዮችም ተግባር ላይ ይውላል፡፡ ሆኖም ሳይንሱ በጣም ጎልቶ የሚታየው ከወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ካየነው በክሪሚናሊስቲክስ እና ፎረንሲክ ሳይንስ መካከል የረባ ልዩነት የለም፡፡ እንዲያውም ለአንዳንዶች ሁለቱም ተመሳሳይ ስያሜዎች ናቸው፡፡

'fornesic' የሚለው ቃል የመጣው forum ከሚል የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉም ህዝባዊ ወይም የህዝብ ማለት ነው፡፡ በጥንታዊ ሮማ ሴኔቱ በፎረም /ህዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ/ እየተገናኘ በፖለቲካና በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ክርክር /debate/ ያካሂድ ነበር፡፡ አሁን ድረስ በተለይ በአሜሪካ በህዝባዊ ክርክር /debate/ የሚወዳደሩ ተከራካሪ ቡድኖች /teams/ "forensics." እየተባሉ ነው የሚጠሩት፡፡

በነገራችን ላይ የመጀመሪያው የፎረንሲክ የሬሳ ምርመራ የተካሄደው እዛው ሮማ ውስጥ ነው፡፡ ጁሊየስ ቄሳር በጠላቶቹ 23 ጊዜ ተወግቶ ሲገደል አንቲሺየስ የተባለ ሐኪም የሬሳ ምርመራ ካደረገ በኋላ ቄሳርን ለሞት ያበቃችው የትኛዋ እንደሆነች ለመለየት ችሏል፡፡ በፎረሲክ ሳይንስ ስር የሚታቀፉ ዘርፎች በጣም በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋና የሚባሉት እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ፡፡

- ክሪሚናሊስቲክስ /Criminalistics/
- ባለስቲክስ (Ballistics/ የጦር መሳሪያ ምርመራ / Firearm examination/
- ፎረንሲክ የአጥንት ምርመራ /Forensic Anthropology/
- ፎረንሲክ የጥርስ ምርመራ / Forensic Odontology/
- ፎረንሲክ የሞት እና ሬሳ ምርመራ / Forensic Pathology/
- ፎረንሲክ ሳይኮሎጂ /Forensic Psycology/
- ፎረንሲክ የነብሳት /insect/ ምርመራ /Forensic Entomology/
- ፎረንሲክ አካውንቲንግ /Forensic Sccounting/
- ፎረንሲክ የአደጋ ምርመራ / Forensic Engineering/
- የመርዛማ ነገሮችና አደንዛዥ ዕፅ ምርመራ /Toxicology/
- ፎረንሲክ ባዮሎጂ /የደም፤ የፈሳሽና ዲ.ኤን.ኤ ምርመራ/ /Forensic Biology/
- ፎረንሲክ ኬሚስትሪ /Forensic Chemistry/
- የአሻራ ምርመራ / Ridgeology/
- የሰነድ ምርመራ / Questioned Documents/
- የወንጀል ስፍራ ምርመራ /Crime-Scene Investigation/ ናቸው፡፡

ለግንዛቤዎ!!

የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ በየሳምንቱ የሚታተም **ሚያዚያ 21/1996 ዓ.ም** ተጀመረ

ረቡዕ -ጥር / 01 / 2016 ዓ.ም

ድሬ ጋዜጣ

**አዘጋጆች**
በጽሎ ኃይሌ
ማቲያስ እንዳለ
እስክንድር ኡስማን

**ፎቶ ግራፈር**
ሰላም አበበ

**ዋና አዘጋጅ**
ሔለን ሽጉጤ
( 09 20 26 49 55 )

**ሌይአውት ዲዛይን**
ሰማን ሙስጠፋ

**የኮምፒዩተር ፅሁፍ**
አለም አስጨናቂ

ስልክ - 025 111 6065
ፋክስ - 025 111 4972 ፖ.ሳ.ቁ 370
ኢ-ሜይል - Info pubbure@yahoo.com
ዌብሳይት - www.direcomm.gov.et
ፌስቡክ - Dire Dawa Geovernement Communication Affairs Bureau (@DDGCAB)

# ሠርጋችንን......

በስንታየሁ እንግዳ

የውርጭ መውጫ ጫፍ ነው የጥር ወር የመጀመሪያ ሳምንታት፡፡ ውርጭ አዘል ብርዱን ጉልበታቸውን ታቅፈው ሲተኙየነበሩ ያንን ብቸኝነት የሚበቀሉበት ወር፣ ከብቸኝነታቸው የሚላቀቁበትና ከነጠላ ኑሮ ወደ አንድነት የሚሸጋገሩበት፣ መስታውት ፊት ቆሞ ከራስ ጋር ብቻ ከመማከር ከአቻዎቻው ጋር ነገራቸውን ፈር ለማስያዝ የሚንደረደሩበትና ቤቶቻቸው የሁለት ሰው ሀሳቦች የሚስተናገዱበት ቤት ለመሆን የተዘጋጀበት ነው የጥር ወር፡፡ ዛሬ ላወራላችሁ የወደድኩት ከአንድነት ወደ ሁለትነት መምጫ መንገድ ስለሆነው ስለ ሰርግ ነው፡፡ ሰርግ ብቻውን ሳይሆን ምላሽ የሚባል ታናሽ ወንድም አለው እናም አንድ ላይ ሲጠሩ ሰርግና ምላሽ ይባላሉ፡፡ አዳሜና ሄዋኔ ለአቅመ ትዳር ከደረሱበት ጊዜ አንስቶ የተጣማጅ ፍለጋቸውን የልባቸውን ዐይን ከፍተው መፈለጋቸው የማይደበቅ ሀቅ ነው፡፡ ምክኒያቱም ‹‹ከአንድ ብርቱ ሁለት መድህኒቱ›› ይሉት ብሂል በሚናገር ማህበረሰብ ውስጥ በማደጋቸው ነው፡፡

‹‹ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፡፡›› የሚለውን የፈጣሪን ትእዛዝ መሰረት በማድረግ በውስጡ ፍለጎት እየተገፋ ወንዱ ሴቷን፣ ሴቷም ወንዱን የራሱ አጣማጅ ለማድረግ ከወሰኑባት እና ደፋ ቀና ማለት ከጀመሩባት ቅፅበት አንስቶ በህልም እውናቸው ሲያወጡና ሲያወርዱ የሚስተዋለው የጥምረታቸው ልዩ ቀን የሆነችዋን ውድ ቀናቸውን እንዴት ማክበር እንዳለባቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ዛሬ በኛ ዘመን የተጀመረ ጉዳይ ሳይሆን እንደየጊዜው እና የአኗኗር ሁኔታ ሲከወን የቆየ ተግባር ነው እንደ እምነቱና እንደየባህሉ ሰርግ ሰርጎ አብልቶና አጠጥቶ ሰው እያየው እና ፀሀይ እየሞቀው በአንድ ጎጆ መጠቃለሉ፡፡

በወረሀ ጥር አካባቢ የሰብል ምርትን መሰብሰብን ተከትሎ ጎተራ ሲሞላ ያኔ በየገጠሩ የሚደረገው የሰርግ ስነ-ስርዓት የፈጠረው ተፅዕኖ እየተንከባለለ መጥቶ ለኛ ለከተሜዎችም ቀን ቆጣሪ አግቢዎች እንድንሆን አድርጎናል ወር መርጠን ከወርም ጥርን፡፡ በርግጥ አሁን አሁን አልፎ አልፎ ይህን የወር ገደቡ ጥሰው በመረጡትና በተመቻቸው ወር ውስጥ ሰርጋቸውን የሚሰርጉ ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፡፡ እንግዲህ ሰርግን ስናነሳ የራሱ የሆነ ስንክሳር ያለውና ቀላሉን መንገድ መምረጥ ላልፈለገ ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑ እሙን ነው፡፡ ደጁ ላይ ግዙፍ ሻኛ ያለው በሬ ጥሎ ከሚያገባው ጀምሮ እንደየደረጃው እና እንደየአቅሙ ያለውን አሟጦ እንዲሁም ካነሰውም ተበድሮና ተለክቶ ለአንድ ቀን ያልሆነ ምን አባቱ በማለት ታዳሚውን ለማስደሰት የሚተጋውን ቤቱ ይቁጠረው፡፡ የቤቱን ቀዳዳ በብዙ የሚሸፍን እና ለዘመድ ወዳጅ የሚተርፍ ጥሪትን አሟጦ ሰርግና ምላሽን መደገስ ትክክል ነው አይደለም ለሚለው እናንተው አንባቢዎቼ ብትፈርዱት እመርጣለሁ ምክኒያቱም ይህ በራሱ አንድ ሌላ ርእስ የሚያስፈልገው ጉዳይ ስለሆነ፡፡ ሌላውና አሳሳቢው ጉዳይ ግን ስለ ሰርጉ ከሚወጣው እቅድና ፕላን ጋር አብሮ ሊታይ ሲገባው የተዘነጋ አንድ ጉዳይን ነው እሱም ሰርጋችንን ከማን? ጋር እና እንዴት? እናከብር የሚል ጥያቄን አንስተን ከውሀ አጣጫችን ጋር በጋራ ለመወሰን አብዛኞቻችን ከተለመደው አካሄድ ውጭ የተለየና የተሻለ መንገድ ለመምረጥ አለመሞከራችን ነው፡፡

ህይወት በጋራ የምንኖራት የኔ ብቻ ብለን ከልለን የማናስቀምጣት በብዝሀነት እንድትተዳደር አድርጎ ፈጣሪ የፈጠራት እና አንዱን ከሌላው በሚያጣምር የተፈጥሮ ህግ የምትመራ ነች፡፡ ይህን ደግሞ ከልጅነት ጀምሮ በየዕድሜ ዘለላዎቻችን የምናየው ኩነት ነው፡፡ ለዚህም ነው ‹‹ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል›› የሚሉት አበው ይህ ደግሞ ለቅርብም ይሁን ለሩቅ ወዳጅ ዘመዱ መቆረስ ለለመደ ህዝብ እንግዳ ነገር አይደለም ቁም ነገሩ ግን ለማን እንዴት ማካፈል? የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ ከፍተኛ ወጪ በሚወጣባቸው ሰርግን የመሳሰሉ ድግሶች ላይ ከማን ጋር ፕሮግራማችንን ብናሳልፍ እና ከነማንስ ጋር ደስ ቢለን ይሻላል? የሚለውን ጥያቄ ማሰቡን ብዙም የምንጨነቅበት ጉዳይ አይደለም ምክኒያቱም እንደተለመደው ከወዳጅ ዘመዶቻችን፣ ከመስሪያቤት ባልደረቦቻችን እና ከጎረቤቶቻችን ጋር ማሳለፍ እንደሚገባ ከቀደምቶቻችን ያየነውና የተማርነው በመሆኑ ማሰቡም አስፈላጊ መስሎ አይታይም ይህ ሲባል ግን አልፎ አልፎ እንዲህ ያለውን ሀሳብ የሚያስቡ የሉም ማለት አይደለም ቁጥራቸው እዚህ ግቡ የሚባሉ እና አልፎ አልፎ የሚከሰቱ መሆናቸው እንጂ፡፡

በዓላትን አስታከው እና የተለያዩ ፕሮግራሞችን ምክኒያት አድርገው በማረሚያ ቤት ያሉ እስረኞች እና ደጋፊና ጧሪ የሌላቸውን አረጋዊያንን ነገሬ ብለው የሚጎበኙ መኖራቸው ቢታወቅም የተቀደሰ ስራ እንደመሆኑ መጠን ብዙ ሊያድግና ሊሰፋ ሲገባው ያለበት ደረጃ ይህን ያህልም አመርቂ አለመሆኑ ይስተዋላል፡፡ ከተቸገሩ ጋር አብሮ ማሳለፍ እና ያለውን ተካፍሎ ቡራኬን መቀበል የሚሰጠው ደስታ ምን ያህል እንደሆነ በመንገዱ ያለፉ ያውቁታል፡፡

በመሰረቱ በዚህ ዘመን ለሰርግ ከመጠን ያለፈና ‹‹ብክነት›› የሚሰኝ ደረጃ ላይ የደረሰ የሰርግ ወጪ ማድረግ በአንዳንዶች ዘንድ የሚከወን ሲሆን አንዳንዶች ልባሞች ደግሞ አግባባዊ በሆነ መንገድና መጠን የሰርግ ወጪያቸውን አስልተው በማውጣት እራሳቸውን ሳይጎዱ ሌላውንም ጠቅመው የሀገሪቷንም ኢኮኖሚ ለማቃወሱ ተግባር የድርሻቸውን ጠጠር ሳይጥሉ ሰርግና ምላሻቸውን በአግባቡ ይከውናሉ፡፡ እንደውም አንዳንድ ሀገራት ዜጎቻቸው ቅጥ ያጣና ለመቁጠር የሚያዳግት ብር የሚወጣበትን ሠርግና ምላሽ ከመከወን እንዲቆጠቡ ህግ አውጥተው ክልከላ እስከ ማድረግ ደርሰዋል፡፡ ለምሳሌ በቻይና ዘመነኛ የሚባሉት ሰርጎች ከቻይናውያን ባህል ከማፈንገጣቸው በተጨማሪ አላስፈላጊ ወጪም ይወጣባቸዋል። በሀገሪቱ ባለስልጣናት እንደ መፍትሄ የቀረበው ሀሳብ ደግሞ ለሰርጎች የሚሆን የመመሪያ ሰነድ ማዘጋጀትና ስነ-ስርአቶቹ ባህላዊውን የቻይና ስርአት የተከተሉ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

ሰርጎች ባህላዊውን መንገድ የተከተሉ ከሆነ የተንዘረጠጠ ወጪያቸውም በዛው ልክ ወደ መሆን ስለሚያጋድል ነው ቻይናዊያኑ ባለስልጣናት ለዚህ ውሳኔ መብቃታቸው፡፡ አሁን አሁን በመላው ዓለም እየተስተዋለ እንዳለው፤ ቻይናውያንም በሰርግ ድግሶቻቸው ወቅት ከቤተሰብ፣ ጎረቤት እንዲሁም ከጓደኞቻቸው የተሻሉ መሆናቸውን ለማሳየት ከፍተኛ ወጪ ለድግስ ከማውጣት እስከ ዓለምን መዞር የደረሱ ተግባራትን ይፈጽማሉ።

ደይሊ ሜል በአንድ ወቅት እንደ ዘገበው ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ የተደረገበት የአለማችን ውዱ የሰርግ ስነ-ስርአት በህንድ ተካሂዷል፡፡ ስነ-ስርዓቱ ላይ የአሜሪካ የፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ተፎካካሪ የነበሩት ሄላሪ ክሊንተን እና ጆን ኬሪ ተጋባዥ እንግዶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ሙሹሮቹ የ27 ዓመቷ አይሻ አምባኒ እና 33 ዓመቱን አናንድ ፒሪማልን ሲሆኑ የጋብቻ ስነ-ስርአታቸውን በሞንባይ ከተማ ፈፅመዋል፡፡ ሞንባይ በሚገኘው ባለ 27 ፎቅ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሰርግ ስነ- ስርዓቱ ተፈጽሟል፡፡ የሙሽሪት አባት ሙከሽ አምባኒ በህንድ የታወቁ ባለሀብት ሲሆኑ ከ41 ቢሊዮን ዶላር በላይ የተጣራ ሀብት እንዳላቸው ተገልጿል፡፡ ለሰርጉ ማድመቂያ መድረክ ላይ የዘፈነችው እውቋ ድምፃዊት ቢዮንሴ ኖውንስ ናት፡፡ በሰርጉ ላይ የቦሊውድ እና የሆሊውድ የፊልም ተዋናዮችን ጨምሮ ታዋቂ ሰዎች ተገኝተዋል ተብሏል፡፡

ውድ አንባቢዎቼ ቁብ ነገሩሰውዬው ምን ያክል ጣሪያ የነካ ሀብት ይኑራቸው ቱጃሩ ለልጃቸው ሰርግ ይህን ያክል ዶላር ሲያፈሱ እዛው በህንድ ምናልባም በአካባቢያቸው ይቀምሰው ይጎርሰው አጥቶ በረሀብ አለንጋ የሚሸነቆጡ ስንት አዛውንትና ህፃናት እንዳሉ ማሰብ መቻል አለመቻል ነው፡፡ ለነገሩ የብሩ መጠን ቀልቤን ቢስበው ወደ ባህር ማዶ አሻቀብኩ እንጂ እዚህም እኛው ሀገር ከመጠን በላይና በኛ ሕዝብ አኗኗር ደረጃ ሲሰላ ‹‹ለስንት ደሃ መቋቋሚያ ይሆን ነበር›› አስብሎ እራስን በሁለት እጅ የሚያሲዝ የብር መጠን ለሰርግና ምላሽ ወጪ ይደረጋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ቅንጦት ለምኔ ብለው ከቪሎና ከሱፋቸው በቀር ሌላውን የተመጠነ/ያልተጋነነ የሰርግ ወጪያቸውን ለህፃናት መርጃ ማዕከላት፣ ለአረጋዊያን መጦሪያ ተቋማት እንዲሁም ድጋፍና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው አካላት የሚሰጡና ብሎም በመጠነኛ ወጪ የሰርጋቸውን ቀን ከላይ ከጠቃቀስኳቸው አካላት ጋር አብረው እህል ውሃ በመቅመስ ቡራኬን ተቀብለውና ለሌሎች ምሳሌ ሆነው የሚውሉ በርካቶች ባይባሉም በመጠኑ አሉ፡፡

ቸርነት በማድረግ ውስጥ ያለ ደስታ በሰርግና ምላሽ ወቅት አቧራው ጨሰና አሞራው በሰማይ ሲያሽ ዋለ ተብሎ በመጨፈር ከሚገኝ ደስታ ለመላቁ በዚህ ሂደት ያለፉ ይመሰክራሉ፡፡ በአስተዳደራችን ያሉ የአዛውንቶች መጦሪያ እና መርጃ ማዕከላት በመንግስት ሳይሆን በግለሰቦች በጎ ፍቃድ ላይ ተሞርኩዘው የተቋቋሙ በመሆናቸው እንደ ልባቸው ችግረኛ አዛውንቶችን ለመደገፍና አይደለም ተጨማሪ ነገር መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት እጅ ሲያጥራቸው ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህ የመንግስትን ኃላፊነት መወጣት ላይ ያሉ በጎ አድራጊ ግለሰቦችን ለማገዝ የየትኛውም ዜጋ ግዴታ መሆኑ እንዳለ ሆኖ መንግስት ደግሞ ከማንኛውም አካል በተሻለ መልኩ ፊት ሳይነሳቸው ካለው ውሱን ሀብት በመቀነስ ሊያግዛቸው ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ የዕድሜ ባለጠጎች ከመንግስትም በላይ ቅሬታቸው ከኛ ከልጆቻቸውና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በመሆኑ በፍቅር የታጀበ እርጥባንን ይዘን ልንጎበኛቸው ግድ ይለናል፡፡

ለዚህ ነው ዛሬ የጥር ወር መግቢያ ላይ ሆኜ ሰርግና ምላሻችንን ከታላላቆቻችን ጋር አቅምን ባገናዘበ ወጪ በምርቃታቸው ታጅበን እንፈፅመው ማለቴ፡፡ በጎነት በአንድ ወቅት የሀገሪቱ ቱባ ቱባ ባለስልጣናት ሲያደርጉት አይተን በሞቅታ የምንከውነውና ወዲያው ደግሞ ከላያችን ላይ የምንጥለው ወቅታዊ ነገር አለመሆኑን መገንዘብ ታላቅነት ነው፡፡ በሰርጋችንም ይሁን በሌሎች ጉዳዮቻችን ከወዳጅ ዘመዶቻችን ጋር መደሰቱ ነውር እንዳይደለ ቢታወቅም ከመንደር ወጣ ብለን እድምተኞቻችንንም ሊያስተምር በሚችልበት ስፍራና በጎነትን ሰንቀን ትናትን ለኛ ዋጋን ከፍለው ዛሬን ያቆዩንን አበውንና ሌሎች ችግረኞችን በማሰብና ከነሱ ጋር ማዕድ በመቁረስ አንድም የደስታችን ተካፋይ በመሆን ትናንታቸውን እንዲያስታውሱ በማድረግ በሌላም ጎኑ ያቺን የኛን የደስታ ቀን የጣመና የላመ በልተው አምላካቸውን አመስግነው እኛንም እንዲመርቁን ማድረግበሰርግና ምላሻችን ወቅት ከተሻለው መንገድ ሁሉ የተሻለ ነው፡፡

በርግጥ በጎነትን ከጥርና ከሰርግና ምላሽ ጋር ወቅቱን ተገን አድርጌ አነሳሳሁ እንጂ ሁሌም እና የትም ሊከወን የሚገባው ስራ ነው፡፡ ደሆች የትም አሉ፣ ችግረኞች በዕድሜና በፆታ ሳይወሰኑ በየቅዬያችን ፈሰዋል፤ በአንድም በሌላ ምክኒያት የተራቡና የታረዙ ሩቃችን አይደሉም በመሆኑም ሁላችንም ሁልጊዜና የትም ቦታ ላይ የበጎነት አምባሳደሮች የደግነት ምሳሌዎች ሆነን መጪውን ትውልድ መልካምነት ምን እንደሆነ እናሳየው፡፡ መልካምነትን ለመኖር መልካም ለመሆን ዝግጁ መሆን በራሱ አንዱና ዋንኛው በመሆኑ አይደለም በሰርግና ምላሻችን በየትኛውም ወቅት ዝግጁዎች ልንሆን ይገባናል፡፡ እኔ አብቅቻለሁ፡፡ በጥርና በቀጣይ ወራት ለመጋባት ደፋ ቀና ለምትሉ ሁሉ መልካም ጋብቻ ይሁንላችሁ አልኩ፡፡ ቸር ሁኑልኝ፡፡

# እኛ . . .

ከገጽ 8 የዞረ

መልስ ሳይሰጠኝ እንዳቀረቀረ ቆየ፡፡፤”ይገርምሀል ፤ በዚህ ዓለም ላይ አሉ የተባሉ ዮኒቨርስቲዎች ውስጥ ቢያንስ ለ 30 ዓመታት ሰርቻለሁ ፤ በስራዬም ምስጉን ነበርኩ፡፡ ካላመንከኝ ይኸው የምስክር ወረቀቴ “ አልኩና አቀበልኩት፡፡ አሁንም እንዳቀረቀረ ነው፡፡ ንቀቱ አናደደኝ “ እኔ እኮ ዝም ስትል ስሌት ላይ ያለህ መስሎኝ ነበር፡፡ ሳትማር እንዲህ ራስህን ጥለህ ሰው ትንቃለህ!”አልኩት ፤ የምር ተናድጄ ፡፡

እሄኔ ቀና ብሎ ፤”ጭንቅላት ትገዛለህ ነው ያልከኝ ?” አለኝ፡፡ በዛው የንዴት አይን እያየሁት አንገቴን በአዎንታ በመነቅነቅ ገለፅኩለት፡፡ ፤” ታዲያ ጭንቅላት ገዥ ከሆንክ እንዴት ስሌት ላይ ያለው ይመስልሀል ? ለማሰብ ጭንቅላት እንደሚያስፈልግ ልትሸጠው ያወጣኸው ጭንቅላት አላሰበልህም ? ፤ ደሞ ራሴን ብጥልም ልቤ ከኔ ጋር ነው ፤ ከኮት እና ከጃኖ እያወዳደርክ ስታየኝ ራሴን ጥዬ ታየሁ፡፡ ያንተ እውቀት በማነፃፀር አንዱን ከፍ አንዱን ዝቅ ማድረግ የሚችል ነው ፤ የቱንም ነገር ያለ ደረጃ መቀበል ባህሪው ስላልሆነ ሁሌም ከሌላው የተለየህ እንደሆንክ ታስባለህ ፤ መልካም ነኝ ለማለት የግድ የሆነ ያኽል የሌላውን መጥፎነት ትፈልጋለህ ፤ እኔ ራሴን ጥዬ እንኳ ከልቤ ጋር በመሆኔ ብቻ ይህ ህይወቴ በቂዬ ሆኗል ፡፡ የምር ነው ምልህ ደስተኛ ነኝ፡፡ “አለኝና አናቱ ላይ የደፋትን ቆብ መሳይ ኮፊያ አነሳት፡፡ ክብ ፀጉር አልባ አናት ብቅ አለ፡፡ከዛም ቀና ብሎ በፈገግታ እያየኝ፤” የሚገርም ህይወት ነው ፤ ጭንቅላት የሌለበት ልብ ብቻውን ሞተር የሆነበት ምርጥ ህይወት ነው፡፡ እውቀት አለህ የምርጥ ሳይንሳዊ ልምድ ባለቤት ነህ፤ ግሩሙ ጉዳይ ግን አሁንም እንደባዘንክ መሆንህ ነው፡፡ ከራስህ ወጥተህ የሚያረካህን ታሳድዳለህ ፤ የተሻለ ነገር ትፈልጋለህ፤ ትመርጣለህያልተሻለ መስሎ የታየህን ትጥላለህ እስቲ ልጠይቅህ እየጣሉ ሙሉ መሆን ይቻላልን?በማንሳት እናበመጣል ህይወት ውስጥ ሙሉ የመሆን ተፈጥሮ ያለ ይመስልሀልን?እባክህን ሰው ያጣው ጭንቅላቱን ሳይሆን ልክ እንዳንተ ልቡን ነው፡፡”ሀይል ለማጠራቀም ነው መሰለኝ አቀረቀረ ፤ በርግጥ ይህንን ትልቅ ሸክም ለማፍረስ ሀይል ግድ ነው፡፡

ቀና አለና በርህራሄ እየተመለከተኝ፤” በህይወት ውስጥ የሚጣል ነገር የለም ፤ ሁሉም ክስተቶች የእግዚአብሔር ጣፋጭ ፍሬዎች ናቸው ፡፡ ስለዚህ ከጭንቅላትህ ከብደህ ከልብህ ብታንስም እሄም የእግዚአብሔር ጣፋጭ ፍሬ የሆነ ክስተት ሲሆን ፤ ከልብህ ከብደህ ከጭንቅላትህ የምታንስበት ሌላ ጣፋጭ ፍሬም አለ፡፡ በእግዚአብሔር ፍሬዎች ውስጥ መራራ የሚባል ፍሬ የለም ሁሉም ጣፋጭ ስለሆኑ ይበላሉ ፡፡ ሆኖም ግን አይን የሚሆኑህ ጆሮ የሚሰጡህ የተለዩ ፍሬዎች ብቻ ናቸው፡፡ አሸናፊ ደስተኛ የሚያደርጉህ ፡፡ ልክ ልብህ ከብዶ ጭንቅላትህ እንደሚያንሰው ማለት ነው፡፡” ሲሉ መከሩት፡፡

# ለለውጥ . . .

ከገጽ 5 የዞረ

የሚበረታታው የራስን ስራ መፍጠርና ማስፋት በዚህም ራስንና ህብረተሰቡን ሀገርንም ተጠቃሚ ማድረግ መቻል ነው፡፡ ያደጉና የበለጸጉ ሀገራትን ወደላቀ የኢኮኖሚ እድገት ማማ እንዲወጡ ታላቁን አስተዋጽኦ ያደረጉት ወጣቶች ናቸው፡፡ ወጣቱ የትኩስ ጉልበትና በፈጠራ ችሎታ የተሞላ አእምሮ ባለቤት በመሆኑ በሀገር ኢኮኖሚው እድገት ውስጥ የላቀ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በጥናትና ምርምሩ በአዳዲስ ስራ ፈጠራዎችና ግኝቶች በግንባታውና በኮንስትራክሽኑ ዘርፍ በዘመናዊ ግብርናው በከተሞች ግንባታና በመሳሰለው ዘርፍ ወጣቱ ወሳኝ የስራ ኃይል ነው፡፡

ወጣት አንተነህ ሰባት አመታትን በተሻገረው የስራ ሂደት ደረጃ በደረጃ እያደገ ነው፡፡ ቀደም ሲል በኤሌክትሪክ በምጣድ ምርት የተጀመረው ስራ ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ምርቶች መሸጫ መደብር ባለቤት ነው፡፡ ቀጣይ የወጣቱ ህልም ስራውን ወደ ከፍተኛ ፋብሪካ ማሳደግ ነው፡፡ ለዚህም ሳይታህት እንደሚሰራ እንቅፋትና ፈተናዎችን በፅናት ለማለፍ ዝግጁ መሆኑን ይናገራል፡፡ እኛም ለባለታሪካችን አንተነህ መልካሙን ሁሉ እየተመኘን ከወጣቱ ታሪክ ልንማረው የምንችለውን የሚገባው በርካታ ልምድ ስላለ እንጠቀምበት ባይ ነን፡፡ መልካም ሳምንት! ደህና ሁኑ፡፡

# ለለውጥ አንድ እንበል

በዳግማዊ ፍቃዱ

ጤና ይስጥልኝ አንባቢያን ባለፈው ሳምንት እትማችን በእንግዳችን አምድ የሁለት ስራ ፈጣሪ ወጣቶችን ታሪክ ማስነበባችን ይታወሳል፡፡ በዚህ አምድ በአስተዳደራችን በተለያዩ ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማ የሆኑ ወጣቶችን ታሪክ ለማስነበብ ቃል በገባነው መሰረት ለዛሬም የአንድ ወጣትን የስራ ታሪክ ይዘን ቀርበናል፡ ፡መልካም ንባብ፡፡

ወጣት አንተነህ አለማየው ከሰባት አመታት በፊት በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ትምህርት በኤሌትሪካል ሙያ ተምሮ ተመርቋል፡፡ወጣቱ ትምህርቱን ጨርሶ ስራ ፍለጋቁጭ አላለም የራሱን ስራ ለመፍጠር ተንቀሳቀሰ እንጂ፡፡እናም በኤሌክትሪክ ምጣድና ሌሎች ተያያዥ ስራዎች ምርት ላይ ተሰማራ፡፡

በአገራችን እንደ ወጣት አንተነህ ሁሉ በርካታ ወጣቶች በተለያዩ ዘርፎች የተመረቁ ቢሆንም አብላጫውን ቁጥር ያለው ወጣት ካለስራ የተቀመጡ ለመኖራቸው እሙን ነው፡፡ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች በስራ አጥነት ተመዝግቦ የሚገኘውን ወጣት ወደስራ ፈጥኖ ማስገባት፤ የራሱን መነሻ አግኝቶ በቀጣይ ስራውን እንዲያስፋና እንዲያሳድግ ማገዝ፤በቸገረውና በጎደለው የባለሙያዎችን ምክርና እገዛ እንዲያገኝ ማድረግ ተገቢም አስፈላጊም ነው፡፡ ወጣቱን ወደ ስራ ለማስማራት ክልሎች የየራሳቸው አካሄድና የአደረጃጀት ስልት ይኖራቸዋል፡ ፡ የወጣቶቻችን ስራን አክብረው መስራት፤ ሰርተውም መለወጥና ለራሳቸውም ለሕብረተሰቡም መጥቀም እንዲችሉ ማድረግም ይገባል፡፡

ወጣት አንተነህ ዜጎች በተለይም ወጣቶች በራሳቸው ሰርተው ለመለወጥ ጥረት ካደረጉ የማይቀይሩት ነገር እንደሌለ የስራው ውጤት ማሳያ ለመሆኑ በርካታ ምሳሌዎችን አጣቅሶ መግለፅ ይቻላል፡፡ ወጣቱ ስራ ሲጀምር እጅግ አነስተኛ በሆነ የካፒታል መጠን እንዲሁም በውስን የሰው ሃይል ነበር፡፡ ወጣቱ እንደሚለው ስራውን ሲጀምር አንድ ሜትር በማይሞላ የስራ ቦታ ነበር ስራውን የጀመረው፡፡ አንተነህ በተሠጠው ሰፊ እድል ያለውን አቅም ተጠቅሞ ለማደግና ለመለወጥ መስራት እንደሚችል ያመለክታል፡፡

ዛሬ ከሀገራችን ሕዝብ ውስጥ 70 በመቶ የሚሆነው ወጣቱ ነው፡፡ እንዲህ አይነት የገዘፈ የወጣቶች ቁጥር በሀገሪቷ ታሪክ ውስጥ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም፤ ይህ ባልተጠበቀ ሁኔታ እያደገ የመጣውን የሕዝብ ቁጥር የሚያሳይ ነው፡፡ ከድህነት ለመውጣት ሰፊ ትግል በማድረግ ላይ ባለች ሀገር ውስጥ የወጣቱ ጉልበትና እውቀት በወሳኝነት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

የግዴታ ይህንን ችግር ሊፈታና ሊሸከም የሚችል ኢኮኖሚም መገንባት ይጠበቅብናል፡፡ ለምሳሌም ብንወስድ በንጉሱ ዘመን አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ኤርትራን ጨምሮ 25 ሚሊዮን ነበር፡፡ በደርግ ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 50 ሚሊዮን ደርሶ ነበር ፡፡ዛሬየኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 103 ሚሊዮን ደርሷል፡ ፡ የሕዝብ ቁጥሩ ይህን በመሰለ መልኩ በስፋት ማደግና መጨመር ኢኮኖሚው ሊሸከመው ካልቻለ በስተቀር ራሱን የቻለ ችግር ነው የሚሆነው፡፡ የሕዝብ ቁጥር አደገ ማለት ኢኮኖሚው አደገ ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም የአደገውን ኢኮኖሚ ሊያቀጭጨው ይችላል፡፡

ችግሩን በመንግስት ላይ ብቻ መደፍደፉ ስራ አልፈጠረም፤ ስራ የለም ምን እንስራ ማለቱ ራሱን ችሎ የሚያመጣው መፍትሄ የለም፡፡ የስነ ሕዝብ ፖሊሲያችን በስፋት መጤን ይገባዋል፡፡ አሁን የምናነሳው ዛሬ ስላለው የሕዝብ እድገት መጠን ነው፡፡ በዚህ የሕዝብ ቁጥር ፈጣን እድገት ከቀጠልን ወዴት እንደርሳለን ብሎ እንደ ሀገር ማሰብም ተገቢ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ እንደ ወጣት አንተነህ ያሉ ዘርፈ ብዙ ወጣቶችን ማብዛት ይገባል፡፡ ወጣቱ ዛሬ ላይ ከራሱ አልፎ ለሌሎች የስራ እድል መፍጠር ችሏል፡፡ በአነስተኛ ደረጃ የተጀመረው ስራው ሰፍቶ ምርታማነቱን እያሳደገው ይገኛል፡፡ የአንድ ስራ ውጤታማነት የሚለካበት መስፈርት አንዱ ስራውን ከፈጠረው ግለሰብ ወይም ቡድን አልፎ ለሌሎች የስራ እድል መፍጠሩ አቅም ነው፡ ፡ይህ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የህዝብ ቁጥራቸው በፍጥነት እያደገ ለሚገኝ አገራት ያለው ኢኮኖሚያዊ





ፋይዳ የጎላ ነው፡፡

ኢኮኖሚስቶች አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በቀጣዮቹ አስርና ሀያ አመታት ከ200 ሚሊዮን ሊዘል እንደሚችል ይተነብያሉ፡፡ የህዝብ ቁጥር መብዛት በራሱ ያለው መልካምና አሉታዊ ጫና አለው፡፡ አሉታዊ ጫናውን መቀልበስ የሚቻለው ደግሞ አምራች የሆነውን ወጣት ሃይል ወደ ስራ ማስገባት ሲቻል ነው፡፡ አለዛ እየጨመረ የሚሄደውን የህዝብ ቁጥር ይሄንን የሕዝብ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን አሟልቶ፤ የተወለዱ ልጆች ሳይቸገሩ፤ በስርአቱ በልተው ጠጥተው ተምረው ለስራ የሚበቁበትን የጤና ዋስትና የሚያገኙበትን ሁኔታዎች የማመቻቸትና የመፈጸም ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የመንግስት ኃላፊነት ቢሆንም፤ ቁጥሩ ከፍተኛ ከሆነ ለመንግስትም ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል፡፡

የሕዝብ ቁጥር እድገት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በስፋት እስካላደገ ድረስ ለሀገርም ለመንግስትም የሚያስከትላቸው ሰፊ ችግሮች አሉ፤ የብዙ ሀገራት ልምድና ተሞክሮም ይሄንኑ ያሳያል፡፡

ቀደም ሲል ለማሳየት እንደሞከርነው ኢኮኖሚው እድገት በማመጣጠን ብሎም ለአምራች ሃይል በተለይም ለወጣቶችየስራ እድል በመፍጠር ረገድ መንግስት ብቻውን መለወጥ የሚችለው አይደለም፡፡ ስራ ፈጣሪዎች በራሳቸው ስራቸውን ከማሳደግ ባለፈ ከኢኮኖሚው ጋር የተጣጣመ የህዝብ ቁጥር እንዲኖር እያንዳንዱ ቤተሰብ የራሱን ሚና ሊወጣ እንደሚገባ ሳይንሳዊ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡

በኢኮኖሚ ያደጉና የበለጸጉ ሀገራት የሕዝብ ቁጥራቸውን የመጠኑት የተንዛዛ ችግርና ድሕነት እንዳይሰፍን አስቀድመው በማስላት ነው፡፡ ልጅ እንደፈለገው ይወለድ በእድሉ ያድጋል የሚባልበት የጥንቱ ዘመን ዛሬ ላይ አይሰራም፡፡ ምን እመግበዋለሁ፤ መጠለያስ አለኝ ወይ፤ ለትምህርት ቤቱስ፤ ለልብሱ፤ ለሕክምናው ምን የተዘጋጀ ነገር አለ? ብሎ ማሰብንም ይጠይቃል፡፡ እንዲያውም በሰለጠኑትና በአደጉት ሀገራት የቤተሰብ ቁጥር እጅግ የተወሰነ ነው፡፡ መውለድ አቅቶአቸው አይደለም፡፡ በቤተሰብም ሆነ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጥረውን ጫና አስቀድመው ማጤን በመቻላቸው ነው፡፡የሕዝብ ብዛትና ቁጥር መጨመር ብሔራዊ የኢኮኖሚ አቅምንም ይፈትናል፡፡ መንግስት ይሄን ጉዳይ በውል አላጤነውም ባይባልም፤ የቤተሰብ ምጣኔ ግን ለሀገርም ይበጃል፡፡

ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ያላቸውን አቅም ተጠቅመው በተሰጥዖዋቸው ውጤታማ ከመሆን ይልቅ ሃሳብና ልባቸው ባህር ማዶ ሲማትርና ለስደት ሲዳረጉ እናያለን፡ ፡ ይሁን እንጂ እንደ ወጣት አንተነህ ያሉ ተስፋን የሰነቁ በመንገዳቸው ሁሉ የሚገጥማቸውን እንቅፋቶች ገሸሽ በማድረግ የነገ ተስፋቸውን ያመቻቻሉ፡፡ ውጣ ውረዶችን እንዲሁም ከፍታና ዝቅታን የህይወት አንድ አካል አድርጎ በመቁጠር በተስፋ ወደፊት መገስገስን የሚላመዱ እነሱ የነገ አላሚ መነፅራቸው ስኬትን እንጂ ውድቀትን አይመለከትም፡፡ሀገርን የሚለውጠው ይህ አቅም ነው። አዳዲስ አስተሳሰቦችን መከተል የሕብረተሰቡን ሕይወት የሚለውጡ ምርምሮችን ማካሄድ ከድሕነት መውጫ መንገዱን በሳይንሳዊ ዘዴ ማስላት መስራት ሁሉ የሚጠበቀው የሀገር ሀብት ከሆኑት ወጣቶች ነው።ወጣት አንተነህ ያሉ የስራው ትርፋማነትም ሆነ የእድገቱ ደረጃ አሁን ላይ አድጓል፡፡ በአገር ሰርቶ ለመለወጥ እንደሚቻል ብሎም በችግሮች ሳይደናቀፉ ውጤታማ መሆን ምንም የሚያግት ነገር እንደሌለ የኔ ታሪክ ማሳያ ነው ይለናል ወጣት አንተነህ ያሳለፈውን ፈተና በእዝነ ልቦናው ዞር ብሎ በመቃኘት፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት አንዱ የስደት ምክንያት የወጣቱ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መጨመርነው፡፡ በሀገሬ ውስጥ ሰርቼ ለመኖር እድል የለኝም የሚለው ስሜትም ከዚሁ ይመነጫል። ለሁሉም አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ እጅግ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘውም፣ 70 በመቶ የሚሆነውን ወጣት ጥያቄ ለመመለስ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም የሚችለውን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በመንግስት ደረጃ ለወጣቱ በማንኛውም መልኩ የገንዘብም ሆነ ሌሎች ድጋፍ ሳይቋረጥ ቢቀርብም ብቻውን ለውጥ መጣል ብሎ ማሰብ ብልህነት የጎደለው ነው፡፡ ይልቁንም የስራ እድል እንዲያገኙ የተመቻቸላቸው ወጣቶች ስራ ፈጣሪ በመሆን ማንኛውንም ስራ በመስራት አዲስ የስራ እድሎችን ለዜጎች የመፍጠር ስራውን የማስፋት ስራ እንዲሰሩ ማስቻል በሂደትም አቅማቸውን እያጎለበቱ ሰፊ የስራ እድሎችን ለሌሎች ዜጎች እንዲፈጥሩ ማብቃት ይገባል፡፡

ወጣት አንተነህ ከዛሬ ሰባት አመታት በፊት ስራ ሲጀምር የነበረው የካፒታል መጠን አነስተኛ ቢሆንም ዛሬ ላይ ከራሱ አልፎ ለሌሎች የስራ እድል መፍጠር የቻለመበት ደረጃ የደረሰው በዘርፉ ለስራ ፈጣሪ ወጣቶች በተለያየ መልኩ ድጋፍ ከሚያደርጉ አካላት ያገኘው የገንዘብ ብድር ምቾችትን ጨምሮ ሌሎች ድጋፎች ድምር ውጤት እንደሆነ ይገልፃል፡፡

ደጋግመን እንዳልነው፣ ወጣቱ በቀድሞ ዘመናት የነበረውን ከመንግስት ብቻ ስራ የመጠበቅ አስተሳሰብን ከአእምሮው ማውጣት አለበት፡፡ በነጻ ኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ ብዙ ስራዎችና የስራ እድሎች የሚጠበቁት በኢኮኖሚው ውስጥ ሰፊ ተሳትፎ ካላቸው የግል ባለሀብቶች ነው፡፡ የመንግስት ተሳትፎ በብዙ መልኩ ውስን ነው፡፡ ስራን መፍጠርም ሆነ ማስፋፋት የግል ባለሀብቶችና የኢንተርፕሬነሮች ድርሻ ስለሆነ ወጣቱ የራሱን ስራ የሚፈጥርበትን ስራን አክብሮ ሳይንቅ ማንኛውንም ስራ የሚሰራበትን ሁኔታ መፍጠርና ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በሀገራችን ወጣቱ በስራው ስኬታማና ውጤታማ እየሆነ ሲመጣ ወደ መንግስት ካዝና የሚመልሰው የሕዝብና የመንግስት ገንዘብ መሆኑን ማጤን ይገባዋል፡ ፡ በመንግስትም ሆነ ሌሎች ባለድርሻ አካላትየሚመቻች የገንዘብ ብድር ወጣቶችስራ ሰርተው እራሳቸውን እንዲችሉበት ከስራ አጥነት እንዲወጡ የስራ ባለቤት እንዲሆኑ ሰርተውም እንዲመልሱ በብድር መልኩ የተሰጠ እንጂ ስጦታ አይደለም፡፡ ይሄንን ገንዘብ ሰርቶ ለመመለስ ብዙ መልፋትና መስራት ከወጣቱ ይጠበቃል፡፡

እንደ ወጣት አንተነህ አባባል ብድር ወስዶ ስራን ሰርቶ ማትረፍ ብሎም ያለብንን ብድር መመለስ እንደ እዳ ሳይሆን እንደ መልካም አጋጣሚ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ወጣቱ በእስከ ዛሬው ስራሂደቱ ስራ ሲጀምር ከወሰደው 280 ሺ ብር ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ስራውን ለማሳደግ ከድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም የገንዘብ ብድሮችን ይወስድ እንደነበር ይገልፃል፡፡ አሁን ደግሞለአራተኛ ጊዜ300 ሚሌየን ብር ብድር ለመውሰድ በሂደት ላይ ነው፡፡

በአገራችን ለወጣቶች የስራ እድል የሚፈጠርባቸው ዘርፎች እጅግ ሰፊ ናቸው፡፡ የተፈጥሮ አቅምን ካየን ወጣቱን ብዙ ስራ ሊያሰራው የሚችል ነው፡፡ በግብርና፤ በከብት እርባታ፤ በንብ ማነብ፤ በከብት ማድለብ፣ በወተት ተዋጽኦ ሽያጭ፣ ለተለያዩ ካምፓኒዎች ወኪል አከፋፋይ በመሆን፣ በማእድን ዘርፍ፣ መዋእለ ሕጻናትና መለስተኛ ትምሕርት ቤቶችን በመክፈት፣ በአሳ እርባታ፣ መዝናኛ ስፍራዎችን ተቀናጅተው በመክፈት፣ ለወጣቱ የሚሆኑ ፊልም ቤቶችን፣ ቤተመጻህፍትን፣ መጻሕፍት ሽያጭን፣ የእንጨት ስራዎችን፣ የብረት ብየዳ ስራዎችን፣ ሸክላዎችና ጡቦችን በማምረት፣ አሸዋና ሲሚንቶ በማከፋፈል፣ በአነስተኛና መካከለኛ ምግብ ቤቶች ስራ ወዘተ ወዘተ ተዘርዝረው የማያልቁ ሰፊ ስራዎች በሀገራችን ውስጥ እንዳሉ በየክልሉ የተደረጉ በአነስተኛና ጥቃቅን ደረጃ ለመሰማራት የሚያስችሉ የኢንቨስትመንት የስራ ዘርፍ አማራጮች መሆናቸው ያሳያል፡፡

ወጣቶች የመንግስት ስራተኛ ከመሆን በበለጠ ለግላቸው እየሰሩ ማደግ መበልጸግየሚችሉበት ሰፊ እድል አላቸው፡፡ ይህንን እድል በአግባቡ መጠቀምም አለባቸው፡፡ ቀደም ባሉ አመታት በሀገራችን ወጣቱን የስራ ባለቤት ለማድረግ በአነስተኛና ጥቃቅን ማህበራት በማደራጀት ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ውጤታማ የሆኑ አልፈውም ሰፊ የስራ መስክ ለወገኖቻቸው የከፈቱ ደረጃቸውም ከፍ ብሎ ኢንተርፕሬነር ለመሆን የበቁ አሉ፡፡

የባለ ታሪካችን ወጣት አንተነህ ልምድና ተሞክሮው ወጣቱ በመንግስት ከታገዘና ከተደገፈ ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ያስተማረ በተግባር ያሳየ ነው፡ ፡ ከዚህም በመነሳት ነው ስፋት ባለው ደረጃ በመላው ሀገሪቱ ወጣቱን ያማከለና ተጠቃሚ የሚያደርግ ስራ ለመስራት ፈንድ ተመድቦ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ያለው፡፡ በሀገራችን ለረዥም ዘመን የተለመደው መንግስት ቤት ተቀጥሮ መስራት ጡረታ ሲወጡም መውጣት ነው፡፡ ከዚህ ሌላ በአብዛኛው የሚታወቅ ነገር አልነበረም፡፡ ዛሬ ይህ ሁኔታ ከመሰረቱ ተለውጧል፡፡

ሀገሪቱ ከምትከተለው የነጻ ገበያ ስርአት አንጻር

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# < < ጀሶ ያበሉን የት ደረሱ? > >

በበድሉ ሀይሌ

ከጥንት ጀምሮ በአገራችንም ሆነ በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች ምግብን ከሌሎች ነገሮች ጋር መደባለቅ የተለመደ ተግባር ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተለይም ነጋዴዎች በትንሽ ወጪ ብዙ ትርፍ የማግኘት ዓላማ በመያዝ ውኃን ከወይን ጋር መደባለቅ፣ ከወተት ውስጥ ቅቤውን በማውጣትና ከውኃ ጋር በመደባለቅ መሸጥ የመሳሰሉት ተግባራት ከጥንታዊ የሮማውያን ሥልጣኔ ጀምሮ ሲታይ የቆየ ተግባር እንደሆነ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በተለይ በአገራችን ምግብን ከባዕድ ነገሮች ጋር መደባለቅ በብዛት እየተስተዋለ ያለ ተግባር ነው፡፡

የአገራችን የመገናኛ ብዙኃን አውታሮችም መሰል ተግባራትን በብዛት ሲዘግቡ ይስተዋላል፡፡ በተለይም በርበሬን ከሸክላ ጋር፣ እንጀራን ከጀሶ፣ቅቤን ከሙዝ፣ ማርን ከስኳር ፣ ሰጋቱራን ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር የመሳሰሉትን ምግብ ነክ ምርቶች ካልተገቡ ባዕድ ነገሮች ጋር መደባለቅን የመሰሉ ተግባራት ሲፈጽሙ የቆዩ አካላትና ተግባሩ ሲፈጸምባቸው የነበሩ ዕቃዎች ጭምር በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ሰፊ ሽፋን ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡ ታዲያ እነዚህ የተያዙ ግለሰቦችና ንብረቶች በሕግ ፊት የሚዳኙት በምን አግባብ ነው? በዚህ ጉዳይየኢትዮጵያ ሕጎች ምን ይላሉ? አተገባበሩስ?

የምግብ ደኅንነት በጠቅላላው፡- ምግብ ደኅንነት ላይ የሚሰጠው ትኩረት በማደግ ላይ ባለ የሰው ልጆች ፍላጎት ውስጥ እየተከሰተ ነው፡፡ ክርስቲያን ኤለንና ፍሬንዝ የተባሉ አጥኝዎች «ኒውትሬሽን ፉድ ሴፍቲ ኤንድ ኮንስዩመር» (አመጋገብ የምግብ ደኅንነትና የሸማቾች ጥበቃ) በተሰኘው ጥናታቸው እንዳረጋገጡት በዓለማችን852 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ከምግብ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ችግሮች በተለይም ጥራቱንና ደረጃውን ያልጠበቀ ምግብ በመመገብ፣ ከምግብ ንጥረ ነገሮች ጋር የተገናኙ ችግሮች፣ ከምግብ እጥረት ጋር በተያያዘ ለሚከሰቱ ችግሮች ተዳርገው እንደሚገኙ ያመላክታሉ፡፡ በዚህም የተነሳ በርካቶች በተለይም ከሳህራ በታች ባሉ አገሮች ቀደም ሲል ባልተለመደ ሁኔታ እንደ ካንሰር፣ ኮሌስትሮል፣ ኩላሊት፣ ደም ግፊትና የመሳሰሉ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች እየተጠቁ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም በዋነኛነት እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል የጥራት ደረጃቸውን ያልጠበቁና ከባዕድ ነገሮች ጋር የተደባለቁ ምግቦች ይገኙበታል፡፡


እዚህ ጋር ሊታይ የሚገባው ደኅንነቱ የተጠበቀ ምግብ ምን ማለት ነው? ሙሉ ለሙሉ ደኅንነቱ የተጠበቀ ምግብስ አለ ወይ? የሚለውን ነው፡፡ ምግብን በጠቅላላው ደኅንነቱ የተጠበቀ (ሴፍ) ነው ብሎ መናገር አስቸጋሪ እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የተጻፉ ጥናቶች ያሳያሉ። ጆርናል ኦፍ ትራንስፎርሜሽናል ሊደርሺፕ የተሰኘው መጽሔት «ፉድ ሴፍቲ ኤንድ ናቹራል ኳሊቲ ፎር ዘ ፕሪቬንሽን ኦፍ ነን ኮሚዩኒኬብል ዲዝዝስ» በተሰኘው ጽሑፉ እንዳስነበበው፣ ሙሉ ለሙሉ ደኅንነቱ የተጠበቀ (ሴፍ) ምግብ አለ ብሎ መደምደም አስቸጋሪ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ ይልቁኑ በተወሰነ ሁኔታና ጊዜ ውስጥ የቀረበው ምግብ ከብክለት የፀዳ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ማጣራቱየተሻለ እንደሆነ የዘርፉ አጥኝዎች ያሳስባሉ፡፡

የምግብ ደረጃ፡- የምግብ ደረጃ አስገዳጅ የጥራት ደረጃበመንግሥት ወይም በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚጣልና ሸማቹ ኅብረተሰብ ላይ ከምግብ ብክለት ወይም ጥራት ጉድለት መነሻነት ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ቀድሞ ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል የአሠራር ሥርዓት ነው፡፡ የምግብ አስገዳጅ የጥራት ደረጃ ዋነኛ ጠቀሜታ በተለይ ተጠቃሚው ከገበያ በሚጠቀማቸው ምግብ ነክ ምርቶች ላይ መተማመን እንዲኖረውና በምግብ ማምረት፣ ማስቀመጥና ማከፋፈል ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰብ፣ ነጋዴዎችና ድርጅቶች እነዚህን አስገዳጅ የጥራት ደረጃዎች አሟልተው ሥራቸውን እንዲያከናውኑና የተባለውን አስገዳጅ ደረጃ የማያሟሉ አካላት ላይ ተገቢውን የዕርምት ዕርምጃ ለመውሰድ ያስችላል፡፡

በኢትዮጵያ አስገዳጅ የምግብ ደረጃ የመስጠት ኃላፊነትና ሥልጣን ለኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተሰጠ ሲሆን፣ ባለሥልጣኑ በአዋጅ ከተቋቋመበት 1970 ዓ.ም. ጀምሮ ለምግብ ነክና ለሌሎችም ምርቶች አስገዳጅ የጥራት ደረጃ የማውጣት፣ የካሊብሬሽን ሥራዎች፣ የጥራት ቁጥጥር፣ የላብራቶሪ ፍተሻና የጥራት ደረጃ ሰርተፍኬት የመስጠትና መሰል ሥራዎችን እንዲሠራ ተልዕኮ በመያዝ በአሁኑ ወቅት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሥር ሆኖ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡

ይሁንና በተለይ ከምግብ ነክ ምርቶች ጋር ተያይዞ የሚሰጡ አስገዳጅ የጥራት ደረጃዎች በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ በምግብነት ጥቅም ላይ የሚውሉ የምግብ ዓይነቶችን ችላ ያለ እንደነበር በተለይ ቀደም ሲል በዘርፉ የተሠሩ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ይልቁንም እንደ እንጀራ፣ በርበሬ፣ ሽሮ፣ ቅቤና የመሳሰሉ በማህበረሰባችን ዘንድ በስፋት ለምግብነት የሚውሉ ምርቶች አስገዳጅ የጥራት ደረጃ ሳይወጣላቸው የቆዩ በመሆኑ፣ ከመሰል የምግብ ዓይነቶች ጋር ተያይዞ የሚነሱ የጥራትና ተያያዥ ችግሮችን በሕግ አግባብ እልባት ለመስጠት የሚደረገውን ጥረት በአሉታዊ መልኩ ተፅዕኖ ሲያሳርፍበት ቆይቷል፡፡ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ መሰል ችግሮችን ለመፍታት በጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን እንጀራን ለመሰሉ በስፋት ጥቅም ላይ የሚውሉ የምግብ ምርቶች ላይ አስገዳጅ የጥራት ደረጃ የመስጠት ሥራ የተሠራ ቢሆንም ከቅንጅታዊ አሠራርና ሌሎች ወደ ኋላ በስፋት በምንመለከታቸው ምክንያቶች የተነሳ ከምግብ ጥራት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጥፋቶችን በሕግ አግባብ የማረም ሥራ ውጤታማ መሆን ሳይቻል ዘልቋል፡፡

ሕጎቻችን፡- የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሰነድን ጨምሮ የአገራችን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ትላልቅ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች የሰው ልጅ



የሰብዓዊ መብት ዝርዝር ውስጥ ምግብ የማግኘት መብትን አካተው ይገኛሉ፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትም በአንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በግልጽ መንግሥት የአገሪቱ መዋዕለ ነዋይ በፈቀደው መጠን ለዜጎቹ ምግብንና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማሟላት የሚያስችለው ፖሊሲ ቀርጾ ሊንቀሳቀስ እንደሚገባ አስቀምጦ ይገኛል፡፡ ይሁንና ምግብ የማግኘት መብት ካለ ጤንነት መብት ብቻውን ሙሉ ሊሆን አይችልምና ምግብ ከማግኘት መብት ጎን ለጎን ዜጎች ጤናው በተጠበቀ ሁኔታ ውስጥ መኖር የሚችሉበትን አግባብ መንግሥት በቻለው አቅም እንዲያመቻች የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 89(8) ላይ በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህንንና ሌሎች የሕገመንግሥት ክፍሎችን በመመልከት መንግሥት ለኅብረተሰቡ ምግብ የሚያገኝበት ብቻ ሳይሆን ጤናማ ምግብ የሚያገኝበትን ሁኔታ መፍጠር እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህንን ዓላማ ለማሳካት የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎችን አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ ያለ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ የወንጀል ድንጋጌ ይዘት ያላቸው ድንጋጌዎችን ያካተቱትን በተለይ የምግብ መድኃኒትና ቁጥጥር አዋጅ (በግንባር ቀደምትነት)፣ የሸማቾች ጥበቃ አዋጅና የኢፌዴሪ ወንጀል ሕጎችን ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ በመጠኑ ለማየት ተሞክሯል፡፡

የምግብ መድኃኒትና ጤና አጠባበቅ አዋጅ፡- ስለ አንድ ስለ ተወሰነ ጉዳይ በልዩ ሁኔታ የሚመለከት ሕግ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ጊዜ ሁሉ ልዩ ሕጎች (Special Laws) እየወጡ፣ በተለይ ለሚነሱ ጉዳዮች መፍትሔ ለመስጠት ይሞከራል፡፡ በያዝነው ጉዳይም ምግብ ነክ ድንጋጌዎች በተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦችና መመርያዎች ተበታትነው ከሚቀመጡ ይልቅ ምግብንና ምግብ ነክ ጉዳዮችን የሚመለከት ልዩ ሕግ ወጥቶ ችግሮችን በዚህ ማዕቀፍ ለመፍታት የተሄደበት መንገድ ምግብ ከሰው ልጆች ሕይወት ጋር ካለው ቁርኝትና ከምግብ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮችም በግለሰቦች እንዲሁም በማኅበረሰብ ጤና ላይ ሊያሳድር ከሚችለው ዘርፈ ብዙ ችግር አንፃር አለ የማይባል ተግባር ነው፡፡

ይሁንና ይህንን በሚመለከት በአገራችን በሥራ ላይ የዋሉት ሕጎች በተለይም አዋጅ ቁጥር 661/09 እና ይህንን አዋጅ አሻሽሎ የወጣው አዋጅ ቁጥር 1112/12 የምግብ መድኃኒትና ጤና አጠባበቅ አዋጆች ሕጎችን በተጠቃለለ መልኩ ከማቅረብ አንፃር አዎንታዊ ሚና የተጫወቱ ቢሆንም፣ በተለይ ሕጉ ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር ጉልህ ክፍተቶች ይስተዋሉባቸዋል፡፡ በተለይም ከወንጀል ድንጋጌዎች አንፃር በአዋጁ ሊካተቱ የሚገባቸው ነጥቦች በተገቢው መንገድ መካተት አለመቻላቸውን ማስተዋል ይቻላል፡፡

እዚህ ጋር በትኩረት የምናየው ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር የመደባለቅ ጉዳይ ነው፡፡ በጣም በሚገርም ሁኔታ አዲሱ የምግብ መድኃኒትና ጤና አጠባበቅ አዋጅ ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር የመደባለቅ ተግባርን የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል አድርጎ አልደነገገውም፡፡ በአገራችን ኢትዮጵያ ይልቁንም በመዲናዋ በአዲስ አበባ በየወቅቱ የምንሰማቸው አሰቃቂና የሰውን ሰብዓዊነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር የመደባለቅ ተግባራት፣ የምግብን ጉዳይ በልዩ ሁኔታ ለመመልከት በወጣው ምግብ መድኃኒትና ጤና አጠባበቅ አዋጅ የወንጀል ተጠያቂነታቸው ያላካተተ መሆኑ ግርምትን የሚፈጥር ነው፡፡

በአዲሱ የምግብ መድኃኒትና ጤና አጠባበቅ አዋጅ 1112/12 አንቀጽ 67 በግልጽ እንደተቀመጠው፣ «ማንኛውም ሰው ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት ደረጃውን ያልጠበቀ ወይም የአስተሻሸግ ጉድለት እንዲኖረው በማድረግ ወይም አስመስሎ በመሥራት ያመረተ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ ያከማቸ፣ በጅምላ ያከፋፈለ ወይም በችርቻሮ የሸጠ ወይም ለኅብረተሰቡ ያቀረበ» ከሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እንደሚያስቀጣ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይሁንና የድንጋጌውን ይዘት ስንመለከተው ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት ደረጃውን ያልጠበቀ አድርጎ ማምረት በወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ቢሆንም፣ ይህ የወንጀል ተጠያቂነት ዕውን የሚሆነው በቅድሚያ ድርጊቱ የተፈጸመው ቁጥጥር በሚደረግበት ምርት ላይ ነው፡፡ ይህ ምርት አስገዳጅ ደረጃ በሚመለከተው ተቋም የወጣለት ሲሆንና ከዚሁ ከተቀመጠለት ደረጃ በታች ሆኖ የተመረተ እንደሆነ ከድንጋጌው መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትለው አስተሻሸግ ላይ ጉድለት ማድረግ ወይም አንድን ምርት አስመስሎ መሥራትን ያካትታል፡፡ እነዚህ ሁሉ ተግባራት የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ቢሆንም በአገራችን በስፋት የሚታየው ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር ደባልቆ ለገበያ የማቅረብ ተግባር በቀጥታም ሆነ ተዘዋዋሪ በሆነ መንገድ የተከለከለ ስለመሆኑ አልተደነገገም፡፡ ይህ ደግሞ አዋጁ መሬት ላይ ያለውን ችግር በሚገባ ያልቃኘ ስለመሆኑ እንዲሞገት አድርጎታል፡፡

በዚህ ነጥብ ላይ ምናልባት በተቃራኒው ሊነሳ የሚችለው ክርክር ደረጃውን ያልጠበቀ ምርት ማምረት፣ የአስተሻሸግ ብልሹነት ወይም አስመስሎ መሥራትን በወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ተግባራት ተደርገው መደንገጋቸው፣ ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መደባለቅንም ያካትታል የሚል ሊሆን ቢችልም፤ አንድን ምግብ ከመነሻው ከደረጃ በታች ነው ብሎ ለመበየን ለምርቱ የተቀመጠ አስገዳጅ ደረጃ ሊኖር እንደሚገባ እሙን ነው፡፡ ምክንያቱም የተቀመጠ ደረጃ በሌለበት ከደረጃ በታች ነው ብሎ ማለት አይቻልም፡፡ በአገራችን ደግሞ አሁን ላይ ከባዕድ ነገር ጋር ተደባልቀው ለኅብረተሰቡ የሚቀርቡ ምግቦች በአብዛኛው በባህላዊ መንገድ ኅብረተሰቡ ለዘመናት ሲያዘጋጃቸውና ሲመገባቸው የቆዩ አስገዳጅ ደረጃ ለማውጣትም ሆነ በደረጃው መሠረት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ለመቆጣጠር አስቸጋሪ በመሆኑ ምግብን ከባዕድ ነገሮች ጋር መደባለቅን በተለየ መንገድ መያዝ እንደሚያስፈልግ ያመላክታል፡፡

የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ፡- በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጁ ከምግብ መድኃኒትና ጤና አጠባበቅ አዋጁ በተሻለ ሁኔታ ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መደባለቅ ለሚለው ሀሳብ በግልጽ ሽፋን የሰጠ ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 30 ንዑስ ቁጥር 10 «ለሰው ጤናና ደኅንነት አደገኛ የሆኑ፣ ምንጫቸው ያልታወቀ፣ የጥራት ደረጃቸው ከተቀመጡላቸው ደረጃዎች የወረዱ፣ የተመረዙ፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈ፣ ከባዕድ ነገሮች ጋር የተደባለቁ የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ማዘጋጀት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ ወይም መሸጥ የተከለከለና የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ተግባር መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

አዋጁ ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መደባለቅን በግልጽ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ተግባር ተደርጎ መደንገጉ እንደ መልካም ጎን ሊታይ የሚገባው ቢሆንም ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መደባለቅ ለሚለው ሐረግ ተገቢው ትርጉም በአዋጁ ላይ ተሰጥቶት አናይም፡፡ ይህ አለመሆኑ ደግሞ ምግብ ከባዕድ ነገር ጋር ተደባልቋል የሚባለው መቼ ነው? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ለምሳሌ የእንጀራ ዱቄት ወይም የጤፍ ዱቄት ከባዕድ ነገር ጋር ተደባልቋል የሚባለው መቼ ነው?

በአንድ ወቅት በአገራችን የዳሰሳ ጥናት በተደረገበት ወቅት የእንጀራ ዱቄትን ከጀሶ፣ ከካሳቫ፣ በቆሎን ከመሳሰሉ ሌሎች የእህል ዘሮች ጋር ተደባልቀው ተገኝተዋል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ ላይ የተሳተፉ የተለያዩ አካላት ለዚህ ሐረግ የተለያ የትርጉምና መረዳት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዓቃቤ ሕግ ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መደባለቅ ማለት ለምግብነት በሚውል ምርት ላይ ሌላ ለምግብነት ሊውል የማይችል ነገር ሲደባለቅ ነው የሚል መረዳት አላቸው፡፡ በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ተቋም ውስጥ በደንበኞች አገልግሎት ምግብ ከባዕድ ነገር ጋር ተደባልቋል የሚባለው ያለ ደንበኛው ዕውቅና ከዋና ንጥረ ነገሩ ውጪ የሚጨመር ሌላ ማንኛውም ውህድ ነው በማለት ይገልጸዋል፡፡

እዚህ ጋር ልንመለከተው የሚገባው ምንም እንኳን የሸማቾች ጥበቃ አዋጁም ሆነ የኢፌዴሪ ወንጀል ሕግ ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መደባለቅን የወንጀልተጠያቂነት የሚያስከትል ተግባር አድርገው የደነገጉ ቢሆንም፣ ምግብ ከባዕድ ነገር ጋር ተደባልቋል የሚባለው መቼ ነው? የሚለው በሕጎቹ ላይ ተገቢው ትርጉም ያልተሰጠው በመሆኑ ሕጉን ለማስፈጸም በተቋቋሙ የተለያዩ ተቋማትና ባለሙያዎች ስለ ጉዳዩ ያለው ግንዛቤ የተለያየ እንዲሆን ይህምሕግን በማስፈጸም ሒደት ውስጥ ጉራማይሌ የሆነ አረዳድ እንዲኖር አድርጓል፡፡

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# የገና በዓል በድሬ ገበያ

በኤደን ሳሙኤል

ወይዘሮ እመቤት ታፈሰ በድሬዳዋ ከተማ ልዩ ስሙ ሳቢያን ዳዊት ጋራዥ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ስትሆን የ4 ልጆች እናትም ናት፡፡ ዛሬ ከወ/ሮ እመቤት ጋር እኔንም ያገናኘን የገና በዓል ገበያ ነው፡፡ ከወይዘሮዋ ጋር ሰኢዶ ገበያ ላይ የበአል አስቤዛን ስትሸምት የተገናኘን ሲሆን በልዩ ሁኔታ በጋዜጣችን ላይ ቃለ መጠይቅ ልሰራት የወደድኩት ደግሞ በወይዘሮዋ ወጣ ያለ የገበያ ድርድር/ስትከራከር/ ነው፡፡

ከሌሎች ዞር ዞር ብዬ ካየኋቸው ገበያተኞች ማለት ነው ወጣ ባለ መልኩ የእንቁላል ግብይት ስታደርግ ትከራከራለች፡፡ እኔም ለዛሬ ታሪኬ ግብአት ይሆነኝ ዘንድ በማሰብ ወ/ሮ እመቤት በግምት ለአንድ ሰዓት አካባቢ ስትከራከር ከገበያ መሀል ቆሜ እየታዘብኩ ነበር፡ ፡ ወይዘሮዋ በዚህ የኑሮ ውድነት፤ ለኛም አስቢልን.... እንዴት አንድ እንቁላል 14 እና 15 ብር ይሸጣል፡፡ አሁን በቅርብ ከሳምንት በፊት 10 እና 11 ብር ገዝቻለሁ እኮ...... በአል መጣ ብላችሁ ነው እንደዚህ ኪሳችንን የምትገፉንና መሰል ነገሮችን........ እያለች በግራና በቀኝ ከተደረደሩት እንቁላል ሻጭ ነጋዴዎች ጋር ትከራከራለች፡፡

በመጨረሻም ከብዙ አሰልቺ ክርክር በኋላ በ14 ብር ሂሳብ 12 እንቁላሎችን ገዝታ እንደጨረሰች ነበረ የዘንድሮ የበአል ገበያ ምን ይመስላል ስል በትህትና ጥያቄዬን ያቀረብኩላት፡፡ የበዓል ገበያ አሁን ላይ በእጅጉ እየፈተነ ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተዳምሮ በጣም እንደከበደ ገልፃልኛለች፡፡

በተለይም ነጋዴዎች ከእለት ወደ እለት ያመጡት እቃ ላይ በአልን በማሳበብ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ ላይ ሲገኙ የቅዳሜና የእሁድ ገበያዎች እንዲሁም በአሉን ተከትለው የተከፈቱት የባዛር ገበያዎችም ያን ያህል ቅናሽ አይታይባቸውም በማለት ወ/ሮ እመቤት ተናግረዋል፡ ፡ ውድ አንባቢያን ለዛሬ በወይዘሮዋ ታሪክ የቢዝነስ አምዳችንን የጀመርኩት ላነሳው ከፈለኩት ማለትም ከበዓልና ከግብይት አንፃር በከተማችን ድሬዳዋ ያለውን ድባብ በብዙም ሳይሆን በጥቂቱ ላስቃኛችሁ ስለወደድኩ ነው፡፡

በቅድሚያ ግን ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን በሰላም ለገና በዓል አደረሳችሁ ለማለት ስወድ በአሉ የሰላምና የደስታ እንዲሆንላችሁ ከወዲሁ የድሬ ጋዜጣ ይመኛል፡፡ በተጨማሪም እንደሁሌውምና እንደተለመደው በዓሉን ስናከበር በመረዳዳት፣ ያለንን በማካፈልና የተቸገሩ ጎረቤቶቻችን በማሰብ እንዲሁም ዓውዳመት ነውና ሰብሰብ ብለን ማክበር እንደሚገባን መናገር ሳይሆን ይሄ ሀሳብ ድሬዎች ላይ የተለመደና የሚታወቅ በመሆኑ ለዛሬም ላስታውሳችሁ በማለት ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም ሀሳብ አረዘምሽ ካላላችሁኝ በዓሉን ስናከበር በተቻለ መጠን አቅማችንን አገናዝበን ቢሆን ይመረጣል ባይ ነኝ፡፡ ብዙ ጊዜ በባዕላት ጊዜ እንደሚስተዋል ያለአግባብ ወጪዎችን በመቀነስና እቤታችን ባፈራው ልክ በአሉን ማሳለፍ ይገባናል የሚል እሳቤ አለኝ፡፡ በርግጥ እንደኛ ኢትዮጲያኖች ባህል ለአውዳመት ዳቦው፣ጠላው፣ዶሮው፣ፍየሉ እንዲሁም ሌሎች የበአሉ ማድመቂያዎች ከጓዳ ሲትረፈረፉ ማየት የተለመደ ጉዳይ ቢሆንም እነዚህም ማድመቂያዎች ግን ለማሟላት ብለን ብድር ውስጥ መዘፈቅ ተገቢ ያልሆነ ጉዳይ ነው፡፡

ይህንንም ያልኳችሁ በምክንያት ነው፡፡ እንደውም ዛሬ በዓል ስለሆነ መዝናናትም በልኩ ማለት ነው ተገቢ በመሆኑ አንድ ታሪክ ላካፍላችሁ/ካዝናናችሁ እግረመንገድም ከተማራችሁበት በመኖሪያ ቤቴ በርከት ያሉ ተከራዮች ሲኖሩ በበዓሉ ቀርቶ በአዘቦት ቀኑም እርስ በእርስ የመፎካከሩ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ይስተዋላል፡፡ ከሁሉም ደግሞ በተለይ ሁለት ጎረቤታሞች ወደሬና መአዛ /ስማቸው የተቀየረ/ ሁሌም በኑሮአቸው መፎካከርን አልፎ አልፎም መጠነኛ መቀናናትን አስተውልባቸዋለሁ፡፡

በዚህም ባሳለፍነው የአዲስ አመት በአል አንደኛዋ ወ/ሮ ወደሬ ማለት ነው፡፡ ለበዓል ከገጠር የባለቤቷ እንግዶች የሚመጡባት ሆኖ ዶሮ ለመስራት እና ለማቅረብ አቅዳ እንግዶቹ በርካታ በመሆናቸው ዶሮ ስላነሳቸው ከእህቷ ጋር በመማከር በጋራ አንዲት ሙክት ፍየል ገዝተው በማረድ ለመካፈል ወሰኑ፡፡



ፍየሏም ተገዝታ ወ/ሮ ወደሬ ደጃፍ የታሰረች ሲሆን ነገሩ ያልገባትና በጋራ የተገዛችው ፍየል የወይዘሮ ወደሬ የግሏ የመሰለቻት ወ/ሮ መአዛም እኔስ ከእሷ በምን አንሳለሁ እሷ ፍየል ገዝታ እኔ እንዴት ዘመን መለወጫን በዶሮ አከብራለሁበማለት ከባለቤቷ ጋር ከፍተኛ የሆነ ንትርክ ውስጥ በመግባትና በማሳመን ባለቤቷ ፍየል እንዲገዛ ታሳምናዋለች፡፡ በኋላም ባለቤቷ ለጊዜው ፍየል የመግዛት አቅም ስለሌለው እና እጁ ላይ ያለውንም ብር ለሌሎች የበአል አስቤዛ ወጪዎች በማዋሉ የባለቤቱን ፍላጎት ለሟሟላት ከባልንጀራውበርከት ያለ ብር ተበድሮፍየሏን ይገዛል፡፡

በኋላም በዓሉ ካለፈ በኋላ ባለቤትየው የመንግስት ሰራተኛ /ወርተኛ/ በመሆኑ ያለበትን እዳ ለመክፈል ወር መጠበቅ ግድ ነበረና ለበአል የባለቤቱን የፉክክር ፍላጎት ለሟሟላት ብቻ በሳምንቱ እከፍላለሁ ብሎ የተበደረውን ገንዘብ በቃሉ መሰረት ባለመመለሱ ሰቀቀን ውስጥ መግባቱን አስተውያለሁ፡፡ በነገራችን ላይ ውድ አንባቢያን ይህ አባወራ ገንዘቡን ባለመመለሱ ምክንያት ወደቤቱ የሚገባው እያመሸ፣ ወደ ስራም ሲወጣ ከወትሮ በተለየ መልኩ በጠዋት ነበረ ብድሩን እስከሚመልስም የዘወትር መንገዱን እንደቀየረም ሰምቻለሁ፡፡

በነገራችን ላይ ይህንን ታሪክ ያጫወተኝ የበዓል ገጠመኝ ምን አለህ ብዬ ጎረቤቴን በጠየኩት ወቅት የወይዘሮ መአዛ ባለቤት ነው፡፡ አመስግኑልኝ ጥሩ መማሪያ ይሆናልና፡፡ አሁን ላይ አባወራው በዓልን በአል የሚያደርገው ከጎረቤት ጋር ተካፍሎ መብላቱ እንጂ መፎካከሩ አይደለም ይላል፡፡

ማንኛውም ግለሰብም ለአንድ ቀን ደስታ ብሎ ወሩን ሙሉ ሰርቶ ለፍቶ ያመጣውን ገንዘብ ማባከን የለበትም ምንም እንኳን በአል የሚያስደስትና የራሱ የሆነ የሚጠበቅ የአከባበር ስርአት ቢኖረውም አቅማችንንና ኪሳችንን ባማከለ መልኩ መሆን አለበት በማለት ይመክራል፡፡ እኔም እዚህ ጋር ከታሪኩ ጋር በተያያዘ ብቸኛ ልለው የምችለው ነገር “ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደጎሮቤቱ አይኖርም ነው”፡፡

ለትምህርትም ለትዝብትም ያህል ታሪኩን በዚህ መልኩ ካካፈልኳችሁ በቀጥታ ወደተነሳንበት ሀሳብ ልመልሳችሁ፡፡

ወ/ሮ አያልነሽ በመንገድ ዳር ላይ ሸራ ወጥረው አትክልቶችን ማለትም ድንች፣ ቲማቲምና ሌሎች ነገሮችን እየሸጡ መኖር ከጀመሩ ስድስት ዓመታትን ያስቆጡ እናት ናቸው፡፡ በዚህ የበአል ገበያም በሶቢላን፣ እንቁላልን፣ የኮባ ቅጠልንና መሰል በአሉን አስታኮ ተፈላጊነት ያላቸውን ግብአቶች ሲሸጡ አግኝተናቸዋል፡፡

ስራው የዕለት ጉርሳቸውን ከመቻል ውጪ ሌላ ትርፍ እንደሌለው የሚናገሩት ወ/ሮ አያልነሽ፤ አንድ ልጃቸውን ለማሳደግ እየተፍጨረጨሩ እንደሚገኙና አሁን ላይ ነዋሪውንም የኑሮ ውድነቱ በከፍተኛ ሁኔታ ስለጎዳው እንደቀድሞ ለበአል የደመቀ ገበያ እንደሌላቸው በምሬት ይናገራሉ፡፡ ወ/ሮ አያልነሽ ከልጃቸው አባት ጋር ከተለያዩ በኋላ ብዙ ውጣ ውረዶች ማሳለፋቸውን፣ በአንድ ወቅትም የቤት ኪራይ መክፈል አቅቷቸው ጎዳና ላይ መውጣታቸውን አስታውሰዋል፡፡

የኑሮ ውድነቱ በዚህ ከቀጠለ አሁንም ቢሆን ጎዳና ላይ መውጣታቸው እንደማይቀርና መንግሥት አሁን ላይ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወገኖችን ታሳቢ በማድረግ በዓላት በመጣ ቁጥር የአስቤዛ ድጋፍ እንደሚያደርግና በዚህም ክቡር ከንቲባ ከድር ጁሀርን አመስግነው፤ ይህ አይነቱ ተግባር ይቀጥል ይላሉ፡፡ በተያያዘም አቅም አለኝ ሰርቼ መኖር እችላለሁ መንግስት የተወሰነ ድጋፍ ቢያደርግልኝ ይላሉ፡፡

በከተማችን ድሬዳዋ አሁን ላይ አብዛኛው ነዋሪ ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር በሚቻልበት ሁኔታ በኑሮ ውድነቱ እየተደቆሰ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ላይ በአላት ሲመጡ ደግሞ ጫናውን ያገዝፈዋል፡፡ በርግጥ የድሬዳዋ አስተዳደር ንግድ ኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የነዋሪዎችን ፍላጎት ለሟሟላትና በተለይም ዝቅተኛው የህብረተሰብ ክፍልን ተጠቃሚ በማድረግ ሁሉም በየአቅሙ በአልን ተደስቶ እንዲያከብር በርካታ ስራዎችን ቢሮው እያከናወነ እንደሚገኝ ታዝበናል፡፡

ለዚህም ደግሞየኑሮ ውድነትን ያረጋጋል የተባለው‹‹የቅዳሜና የእሁድ ገበያ››ተቋቁሞ ወደስራ ከገባ አመታት ቢቆጠርም ነዋሪው ግን በገበያው ላይ ክፍተቶች እንዳሉ ይናገራሉ፡፡ የተቀጣሪው ደመወዝ ለዓመታት ያህል ባልጨመረበት በሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ የሰብልና የአትክልት አቅራቢዎች፣ የጅምላ ነጋዴዎችና በምግብ ማቀነባበሪያ የተሰማሩ ፋብሪካዎች እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማሳተፍ በየሳምንቱ የእሁድ ገበያን በከተማዋ በተመረጡቦታዎች በማቅረብ እንዲሁም የመሠረታዊ ፍጆታ ሸቀጦች ለከተማችን ነዋሪ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የኑሮ ውድነት ችግር ለማቃለል ጥረትእየተደረገ መሆኑን ጥሩ ጅምር ቢሆንም እየታየ ያለው ውጤት ግን ቅሬታዎችን አስተናግዷል፡፡

አሁን ላይም በዓሉን ተከትሎ በዚህ የቅዳሜና የእሁድ ገበያ ምንም እንኳን የአቅርቦት ችግር ባይኖርም በርካታ ነዋሪዎች ግን የአብዛኞቹ ግብአቶች መንደር ውስጥ ከሚሸጥበት የዋጋ መጠን የቀነሰ እንዳልሆነ ይናገራሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የድሬዳዋ አስተዳደር ንግድ ኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ገበያው ላይ በተጨባጭ የሚታየውን ክፍተት ለመድፈንና በተለይም በዚህ በበአል ሰሞን ከአቅርቦት ጥራት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ለመድፈን ጠንከር ያለ ቁጥጥር በማድረግ እየሰራ እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን ከዋጋ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመድፈንም እቅዶችን በማቀድ እየሰራ እንደሆነ ተገልጧል፡፡

አሁን ደግሞ ውድ አንባቢያን ጠቅለል ባለ መልኩ በከተማችን ያለውን የበዓል የገበያ ድባብ ላካፍላችሁ፡ ፡ የመጀመሪያ ቅኝታችንን ያደረግነው በድሬዳዋ እድሜ ጠገቡና በቅርስነት በተመዘገበው የቀፊራ የገበያ ማዕከል ነው። በዘንድሮው የገና በዓል በርግጥ በድሬዳዋ ከተማ የአቅርቦት ችግር ባይስተዋልም ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ በተለያዩ የኩድራ/አትክልት ምርቶች ላይ እንደተከሰተ ይስተዋላል፡፡

የበዓሉ ዋና ማድመቂያ የሆነው የሐበሻ ዶሮ እስከ አንድ ሺብርና ከዛ በላይ የጥሪ ዋጋ ሲኖረውም አስተውያለሁ፡፡ሌላው ከተማችን ድሬዳዋየምትታወቅበት የእጣን ገበያን ስንመለከት የባህር እጣን በኪሎ እስከ 800 ብር፣ የኡጋዴኑ 600 መቶ ብር እንዲሁም የቅርፊት እጣን 500 መቶ ብር በኪሎ እየተሸጠ ይገኛል። ውድ አንባቢያን እንደሚታወቀው የገበያ ሁኔታ ከቦታ ቦታ ከሰአት ሰዓት የዋጋ መለዋወጥ ያለው በመሆኑ እዚህ ጋር የተጠቀሱት ዋጋዎች አንፃራዊ እንደሆኑ ልብ በሉልኝ፡፡

በቀፊራ የገበያ ስፍራ ያገኘናቸው ወ/ሮ አለም ጉልላት የአቅርቦት ችግር በሌለበት ሁኔታ በተለየ ሁኔታ የሽንኩርትና የቲማቲም ዋጋ በዚህ ደረጃ መወደዱ ግራ እንዳጋባቸው ይገልጻሉ። የጤፍ ነጋዴዋ ወ/ሮ ሀሊማ መሀመድ በበኩሏ ለበዓሉ በጤፍ ላይ ምንም አይነት የዋጋ ጭማሪ እንዳልተደረገ እና የገበያ ሁኔታውም የተረጋጋ እንደሆነሀሳቧን ታጋራለች፡፡ ቀጣዩን ቅኝት ያደረግነው ‘ጀላባ’ ተብሎ በሚጠራው የድሬዳዋ ትልቁ የከብቶች መሸጫ ስፍራ ነው። በጀላባ በግ፣ ፍየል እንዲሁም ሰንጋ በሬ በስፋት ይታያል፡፡ ዋጋቸውም ከዘመን መለወጫ አንፃር ሲታይ ያን ያህል ጭማሪ አለው የሚባል እንዳልሆነ የሰንጋ በሬ ነጋዴ የሆኑት አቶ አወል አሊ ይናገራሉ፡፡

በዘንድሮ የበዓል ገበያም ከበአሉ ከሳምንታት ቀደም ብሎ በተለይም የፍየል ገበያ እንደተጀመረና የበሬ ገበያ ደግሞ በብዛት የመንደር ቅርጫ አቃራጮች ገበያውን ለማጥናት እየመጡ እንደነበረ አቶ አወል ጠቅሷል። ለአቶ አወል ከኑሮ ውድነቱ አንፃር እሳቸው እየሸጡአቸው የሚገኙት ከብቶች ዋጋቸው ምን ያህል ተመጣጣኝ እንደሆነ ጥያቄ ያቀረብንላቸው ሲሆን “በርግጥ የኑሮ ውድነቱ የሁላችንም ራስ ምታት ነው ቢሆንም ግን ማንኛውንም ነገር ስንገዛ ገንዘባችንን በማውጣታችን የማንፀፀተው የእቃውን ጥራት አይተን ነው።

ስለዚህም በኔ በኩል የማቀርባቸው በሬዎች ጤናማ፤ በአመጋገብም በደንብ የተያዙና ለገበያ ከመቅረባቸው ከወራት በፊት ሲቀለቡ የቆዩ ናቸው። የወፈሩትም ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ ነው። ለዚህ ደግሞ ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ ነው የምንጠይቀው” በማለት ነው የመለሱልን አቶ አወል። በመጨረሻም አቶ አወል በስራ ጉዳይ ለሚያውቋቸው ባልደረቦቻቸው እንዲሁም ለመላው የክርስትና እምነት ተከታይ ለሆኑ ኢትዮጵያዊያኖች በሙሉ መልካም የገና በአልን እመኛለሁ በማለት ሀሳባቸውን አሳርገዋል።

ውድ አንባቢያን የበአል ድምቀት ናቸው ብዬ ያሰብኳቸውን በተለይም ከገበያ አንፃር ያሉትን በከተማችን ተዘዋውሬ በመዳሰስ በመጠኑም ቢሆን በድሬ ያለውን የገበያ ድባብ አስቃኘኋቹሀለሁ ብዬ አስባለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ የበአል ወጪያችን እንደቤታችን መሆን ይገባዋል። ለአንድ በዓል የወራት ኢኮኖሚያችን መናጋት እንደሌለበት በማሰብም አጠር ያለ ታሪክ አጫወትኳችሁ።በዓል ነውና ነገር ሳላረዝም የዛሬን በዚህ ላብቃ።በመጨረሻ ግንለመላው የድሬዳዋቸን ነዋሪዎች በአሉን በመረዳዳትና የተቸገሩ ወገኖችን በማሰብ እንዲያከብሩት አደራ እላለሁ። የሳምንት ሰው ይበለን።

**መልካም የገና በዓል!**

## የገናን . . .

ከገጽ 1 የዞረ

በሽታው በሰውነት ውስጥ የሚገኘውን ፈሳሽ በማሟጠጥ አቅምን የሚያዳክም በመሆኑ ሁሉም ነዋሪ ያልበሰሉ ምግቦችን ባለመብላት፣ የግልና የአካባቢ ንፅህናን በመጠበቅ፣ ንጽህናውን ያልጠጠበቀ ውሃ ባለመጠጣት እንዲሁም ሜዳ ላይ ባለመፀዳዳት በሽታውን መከላከል እንደሚገባም ኃላፊዋ ጠቁመዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘም ማንኛውም ሰው በአጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት በማንኛውም ጊዜ ሲከሰት እንዲሁም የበዓል አመጋገብን ተከትለው የጤና እክሎች ሲያጋጥሙ በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ አስፈላጊውን ህክምና ማድረግ እንደሚገባ ዶ/ር ጽጌሬዳ ተናግረዋል።

**በኤደን ሳሙኤል**

**ፎቶ:-አብይ ሽመልስ**

# እኛ እና ፅርሐአሪያም/ዩኒቨርስ

በዘመድ ቢሆነኝ

እስቲ ወደ ዋናው ሀሳቤ ከመግባቴ በፊት እንደመግቢያ ይሆነን ዘንድ ከዚህ ቀደም በራሴ ህይወት ውስጥ ሆኖ ያለፈ አንድ ታሪክ ላንሳ:: ታሪኩም የከተማችንን (የድሬደዋ) አየር ንብረት በእኔ እድሜ እንደተለወጠ የምታሳይ ናት::

የድሬዳዋ የዓየር ንብረትን ከወይና ደጋነት ወደ በርሀማነት ያሸጋገረችው ባለፉት ሁለት አስርት አመታት ውስጥ ነው:: ትዝ ይለኛል በ2002 ዓ.ም የ5ተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ:: ፈተና ላይ ነበርን፤ የፈተናው ጥያቄ የድሬዳዋ አየር ንብረት ምን አይነት ነው ይልና ከስሩ አራትአይነት አማራጮችን ይሰጣል:: ከነዚህ አራት ምርጫዎች ውስጥ በርሀማ እና የወናደጋ የሚሉ አማራጮች አሉ:: ሁላችንም ማለት ይቻላል የወይና ደጋ የሚለውን ነበር የመረጥነው:: ጥያቄው ታርሞ ሲመጣ ግን ሁላችንም ተሳስተን ነበር:: ፤"እንዴት ይሆናል??!!"ብለን ወደ መምህራችን ሄደን ጠየቅን: : መምህራችን ጥሩ ሰው ነበሩ፤" ጥያቄው ከተወሰኑ አመታት በፊት ቀደም ብሎ ተጠይቆ ቢሆን ኖሮ ልክ ትሆኑ ነበር:: አሁን ግን የከተማችን አየር ንብረት ወደ በርሀማነት ስለተለወጠ ልትሳሳቱ ችላችኋል::" አሉን በትህትና:: ይህን ጥሬ ሀቅያነሳሁት ከስር ለማነሳው ሀሳብ እንደማጣቀሻ ይሆነኝ ዘንድም ነው ::

ብዙ ሰው ህይወት ምርጫ እንደሆነች ያስባል:: ማሰብ ብቻ ሳይሆን ይህንን እንደመርህ አምኖ ተቀብሏል: : የማመኑ መጠንም ሌላ እውነት ሊኖር እንደሚችል እስኪዘነጋ የሚደርስ ሆኗል:: በዚህም በህይወት የመምረጥ ግዴታ እንደሚኖር የሆነ የተሻለ ነገርን አመዛዝኖ መምረጥ ካልተቻለ ህይወት አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል የብዙ ሰው ቀኖና ሊሆን በቅቷል::

ፍቅረኛን በተመለከተ ፣ ስራን በተመለከተ ፣ የኑሮ ቦታን በተመለከተ ፣ ጓደኛን በተመለከተ ፣ የእለት ድርጊትን በተመለከተ ብዙ ሰው የተሻለ ለመምረጥ እንደፔዱለም ሲወዛወዝ ይውላል:: ለመምረጥ ተጨንቆ መስፈርት ያወጣል:: የትዳር አጋሩን ሳይቀር በብዙ መስፈርቶችና በብዙ ፈተናዎች መዝኖ መምረጥ ይሻል፤ ለኔ እሄ ሁሉ ሩጫ አላስፈላጊ ነው:: ህይወት ለኔ በጣም ቀላል፥ ያልተወሳሰበች ልክ እንዲዚህ ፅሁፍ ርዕስ ነፃነቷ በምርጫ አልባነት ውስጥ የሚከሰት አስደሳች የለት ኑሮ ነች::

ሁሉም ሰው አንድ መርሳት የሌለበት ጥሬ ሀቅ አለ: : አሁን ዮኒቨርስ (ፅርሐአሪም) ላይ ተገልጦ የሚታየው ህይወት ያለውም ይሁን የሌለውም ፍጥረት ገና እድገቱ እንዳላበቃ እና ሁሉም ነገር እድገት ላይ፥ ለውጥ ላይ ያለ መሆኑን መርሳት የለበትም:: ሌላው ቀርቶ ግለሰቡ ራሱ በእድገት ላይ ፣ነገ ሌላ በመሆን ላይ ያለ ፣ ከውልደት እስከ ሞት የሚያድግ ፣ የሚለወጥ መሆኑን በጭራሽ ሊዘነጋ አይገባውም:: ሰው ሞቶ እንኳ የእድገት ፣የለውጥ ፣ የመሸጋገር ተፈጥሯዊ ሂደቱን ለአፍታ አያቆምም:: እና በአጭሩ የመፅሐፍ ቅዱስ 7ኛው ቀን ገና አልደረሰም: : ሁሉም ነገር በመፈጠር ላይ ነው ፤ ዮኒቨርስ ገና በመወለድ ላይ ነው:: ስለዚህ ምርጫ ለእንዲህ አይነቱ ህልውና ከንቱ ድርጊት ነው::

በእንዲህ አይነቱ ህልውና (ዮኒቨርስ) ውስጥ እያሉ ምርጫ ስለሚያደርጉ ሰዎች አንድ ነገር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል:: በመረጡት ነገር እንደማይረኩ ፣ ወደው የመረጡትን ነገ በሌላ ምርጫ እንደሚሸሩት ፣ ህይወታቸው ሁሉ አንዱን በማንሳት ሌላውን በመጣል የተሞላ እንደሆነ መናገር ይቻላል::ሁሌም እነሱ ጋር የሚሞት እና የሚያረጅ ነገር አይጠፋም:: ፍቅር ሳይቀር ያረጃል:: ምክንያቱም የፍቅርን ወጣት መሆን ስለሚመርጡ ያረጅባቸዋል:: ደስታን ጠዋት መርጠው ከሰዓት በሀዘን ይዋጣሉ:: ሰላምን መርጠው እረፍት አልባነትን ያገኛሉ:: እንዲህ አይነት ሰዎች እንግዲህ ከህይወት መሰረታዊ ቁም ነገር የራቁ ገና ህይወት አለመምረጥ እንደሆነ ያልተረዱከብዙኋኑ ጋር አብረው የሚነጉዱ ተራ ፍሳሾች ናቸው::

ለመረዳት ይቀል ዘንድ እስቲ ደረጃ በደረጃ ሀሳቤን ላስቀምጥ:: አንዱን መርጦ ሌላውን በመተው ህይወት ውስጥ ሙሉ የመሆን ተፈጥሯዊ መብት እንደሌለ ግልፅ ነው:: ፍጥረት በማያቋርጥ ዑደት ውስጥ መኖሩን የማይቀበል የለም:: ውልደት እና ሞት የማያቋርጡ የተፈጥሮ ክስተቶች እንደሆኑ ክርክር የማያስነሳ ሀቅ ነው: : ሁላችንም ዑደት እንዳለ እና ሁሉም ነገር ከውልደት ወደ ሞት ፥ ከሞት ወደ ውልደት እንደሚንቀሳቀስ እንስማማለን:: ቋሚ የሚባል ክስተት እንደሌለም ተመሳሳይ ግንዛቤ አለን:: እስከዚህ ድረስ ከተስማማን ቀጣዩን እና ይህ አይነቱን የዩኒቨርስን እውነታ ከመምረጥ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልጠውን ሀሳቤን በግልፅ ለመረዳት ይቀላል:: እናንተ ሀሳቡን በግልፅ ለመረዳት ጥረታችሁን ቀጥሉ ፤ እኔ ደሞ ማብራራቴን እቀጥላለሁ::

ዮኒቨርስ ተለዋዋጭ እና በመሞት እና በመወለድ እንቅስቃሴ ውስጥ ነው:: <ዮኒቨርስ> ስንል ከኛ ውጪ ያለ እኛ የምንኖርበት ሳይሆን ፤ እኛ አንዱ የአካል ክፍሉ የሆንበት ፣ ሌሎች ብዙ ፍጥረቶችን አካሉ ያደረገ ፣ የነዚሁ ተፈጥሮዎች ስብስብ የሆነውን ሁለንተና ማለታችን ነው:: <ዮኒቨርስ ይሞታል ይወለዳል> የሚለው አረፍተ ነገር ዮኒቨርስን ሙሉ ያደረጉት ፍጥረታት ይሞታሉ፤ ይወለዳሉ የሚለውን ማጠቃለያ የሚሰጠን ነው::

ይህ ሁለንተና በእንዲህ አይነቱ ባህሪው የተነሳ ሳይንሳዊ ህጎች ሳይቀሩ ቋሚ መሆን ተስኗቸው በባለፈው ዘመን <እውነት> የነበሩት ህጎች በዚህኛው ዘመን ደሞ <ውሸት> ሲሆኑ ታዝበናል:: ሁሉም ነገር የሚለወጥ ነው:: ልጅ የነበረው ወጣት ይሆናል ፤ ወጣት የነበረው ይጎለምሳል እንዲሁም የጎለመሰው ያረጃል:: ከዋክብት ወደ ሁለንተና ምንምነት ውስጥ ጠፍተው ከዛው ሁለንተና ምንምነት ውስጥ ይወለዳሉ:: ደን የለበሱት አካባቢዎች በርሀ ይሆናሉ:: ከመግቢያው ላይ ያነሳሁትን <የድሬዳዋን አየር ንብረት> ልብ ይሏል::

በዚህ አይነቱ ዮኒቨርስ ውስጥ እኛም እየኖርን ነውና የመለዋወጥ እጣው እኛም ላይ መውደቁ የማይቀር ነው: : በአካል ብቻ ሳይሆን በባህሪ እና በስሜት ደረጃም መለዋወጣችን የግድ የሆነ ያኽል በየለቱ የሚከሰተው ስውር በሆኑ የኢነርጂ ሰንሰለቶች ከተቀረው እና ተለዋዋጭ ከሆነው ሁለንተና ጋር ስለተሳሰርን ነው:: ይህ ማለት ግልፅ ነው:: ይህ ጫፍ አልባ አድማስ እና በውስጡ ያሉት ፍጥረታት ያለ ሁለትነት በአንድነት የቆሙ ናቸው:: የአንዱ እንቅስቃሴ ሌላው ላይ ተፅዕኖውን ያሳርፋል:: ጠዋት ፀሀይ ስትወጣ ሁሉም ከተጋደመበት ይነሳል፤ እንስሳቶችም ከዋሻዎቻቸው እና ከጎሬዎቻቸው ይወጣሉ ፤ እፅዋቶችም ይፈካሉ:: ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሁለንተና የተሳሰረማንም ብቻውን ያልቆመ እንደሆነ ነው:: በዚህም ሳቢያ ተለዋዋጩ ዮኒቨርስ የመለዋወጥ ባህሪውን ሊያወርሰን ችሏል:: እኛም በሰዓታት ልዩነት የምንለዋወጥ ሆነናል::

የየትኛውም ፍጥረት እንቅስቃሴ የማይሰማው የሆነ አይነት ስሜት የማይፈጥርበት የሰው ልጅ የለም:: ንፋስ ሲነፍስ ወይ የመበሳጨት ወይ ደሞ የመደሰት ስሜት የማይሰማው ሰው ተፈልጎ ለማግኘት ይቸግራል: : ሁላችንም አንድ ነን ፤ በሰው ልጅነት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ፍጥረታትነት አንድ ነን:: ይህ አንድነት ተወልዶ የሚሞተውን መልሶ የሚወለደውን የዚህን ዮኒቨርስ ባህሪ ሁሉም ፍጥረታት እንዲወርሱ እና አካሉ እንደሆኑ የሚያስገነዝብ በቂ አስረጅ ነው::

ከላይ ጀምሮ እንዳስረዳሁት ምርጫ ማድረግ ሰዎች የግድ የሆነ ያኽል ተቀብለውታል:: ከሁለት ነገሮች አመዛዝኖ አንደኛውን መርጦ ሌላኛውን መጣል የተለመደ የእለት ሩጫ ነው:: ግን ዛሬ ጥሩ የሆነው ነገ መጥፎ በሚሆንበት፥ ዛሬ አለ ያልነው ነገ የለም በሚሆንበት ዮኒቨርስ ውስጥ ሆነን ፥ የኛም ስሜት እና ባህሪ ያለማቋረጥ በሚለወጥበት ሁኔታ ውስጥ አመዛዝኖ መምረጥ የሚባለው ድርጊት ትክክለኛነቱ እስከምን ድረስ እንደሆነ ጥያቄ የሚያስነሳ እና ትክክል ስለመሆኑም የሚያጠራጥር ነው::

በስሜት ከፍ እና ዝቅ ማለት ፣ በኑሮ መዋከብ ፣ በሩጫ የሚባክን እለት ሁሉ የሚመጣው የራስን እና የዮኒቨርስን ተለዋዋጭ ባህሪ ካለመረዳት እንዲሁም ህይወት ፍሰቷን ጠብቃ ትጓዝ ዘንድ እንዴት መቀበል እንዳለብን ካለማወቅ ነው:: ምክንያቱም ሁሉም ሰው የሚመርጠው የህይወት ቆይታውን የሰመረ ለማድረግ ነው:: መምረጥ የህይወትን ያልተዛባ ጉዞ ለማሳካት ተብሎ አገልግሎት ላይ የሚውል ዘዴ ነው::

መወሰን እንዳለብህ ሁሉ መምረጥም ይኖርብሀል: : ሁለቱም ለህይወት መቃናት የሚያገለግሉ የሰው ልጅ ዘዴዎች ናቸው:: ልክ ለመመገብ እጃችንን ፣ ለመራመድ እግራችንን እንደምንጠቀመው ማለት ነው:: የመመገቡ ሂደት የሰመረ እንዲሆን እጅ አልግሎት ላይ ይውላል: : ምግቡን የሚያነሳበትም የራሱ የሆኑ ዘዴዎች አሉት: : ስለዚህ የመመገብን ሂደት ለማቃናት እጅን እንደ ዘዴ ስንጠቀም የህይወት ፍሰት የተስተካከለ እንዲሆን ደሞ <መምረጥን> እንደ ዘዴ እንጠቀማለን::

ለህይወት መቃናት የተሞከሩ ዘዴዎችን መጠቀም ተገቢ ነው:: ነገር ግን በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ብዙ የተዛቡ ተሞክሮዎች አሉ:: ይህም ማለትንቁ ያልሆኑ ሰዎች በሚኖሩት ህይወት ከህይወት ጋር የሚኖራቸው ቁርኝት የደበዘዘ እና ጥልቀት የጎደለው ስለሚሆን የሚያገኙት ተሞክሮ የሚመስለውን እንጂ የሆነውን አይደለም:: እንደነዚህ አይነት ሰዎች በሚነግሩን ተሞክሮዎች የተነሳ የሰው ልጅ ያልተዛባ ብቻ ሳይሆን የተዛባም ተሞክሮ ባለቤት ለመሆን ችሏል:: ከነዚህም የተዛቡ ተሞክሮዎች መሀከል እንዱ እንግዲህ <የመምረጥ> ተሞክሮ ነው:: ስለዚህ ይህን የተዛባ ተሞክሮ ማስተካከል ያስፈልጋል: : ካልመረጥን እንዴት የተሻሉ ነገሮች ወደኛ ሊመጡ ይችላሉ? ብላችሁ መጠየቃችሁ አይቀርም እኔም እንዴት ከምርጫ የፀዳ ነፃ የሆነ ህይወት ሊኖረን እንደሚችል በተቻለኝ መጠን አስረዳችኋለሁ::

በመጀመሪያ ያለንበትን የዩኒቨርስ ባህሪ መረዳት:: ምንኖርበትን አውድ ባህሪ ከተረዳን የሁሉንም ፍጥረታት አንድነት መረዳት ብዙ አይከብደንም:: ይህን የአንድነት መረዳት ተከትሎ የሚመጣ የባህሪ መወራረስ ግንዛቤ ይኖረናል:: በዩኒቨርስ ሞት እና መወለድ ውስጥ የኛም መሞት እና መወለድ መኖርን መገንዘብ እንችላለን:: የኛን መወለድ እና መሞት ካስታወስን ደሞ ውጫዊ ምርጫዎች ከእንዲህ አይነቱ የህይወት ባህሪ ጋር የማይጣጣም እንደሆነ ይገባናል::

ሰው የኑሮ ግቡ ደስተኝነት ከሆነ ደስታን የሚያገኘው መምረጥ ያቆመ ቀን ነው:: ሁሉንም ያለምንም ወዳጅነትጠላትነት መቀበል የጀመረ ለት ህይወት ደስታዋን ትሸልመዋለች:: ምርጫ ውስጥ ሁሌም ወሰን አለ፤ አለመምረጥ ውስጥ ደሞ ገደብየለሽነት አለ:: ታዲያ ልብ በሉ ይህ ዮኒቨርስ መጨረሻ አልባ፣ተለዋዋጭ እና ገደብየለሽ ነው:: ወደ ትክክለኛው የሁለንተና ባህሪ ስንገባ በህይወት ደስተኛ ለመሆን እና የሰመረ ህይወት እንዲኖረን ለማድረግ የምንችል እንሆናለን:: የዮኒቨርስ ትክክለኛው ባህሪ ደሞ ገደብ የለሽነት እና ዑደታዊ(የማያቋርጥ ለውጥ) ነው:: እመኑኝ ቀናችሁን በፈገግታ መኖር ከፈለጋችሁ ውጫዊ ፍላጎቶቻችሁን በሙሉ እንዲመክኑ አድርጉና የማትመርጡ ሁኑ:: ህይወት ያኔ ከምርም የደስታ አዝመራ የሚታጨድባት አውድማ ትሆናለች::

እሄ አነ አፍላጦን እና አሪስጣጣሊስ ፍፁማዊውን ማህበረሰብ ለመገንባት የወጠኑት <የዩቶቢያ> ፅንሰ ሀሳብ አይደለም:: ሊተገበር የማይችል ምናብ አይደለም:: እሄ ተጨባጭ መሆን የሚችል በዓለማችን ላይ ብዙ ሰዎች በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብም ደረጃ ሊኖሩት የቻሉት ቁም ነገር ነው:: ሀሳቡም በጣም ቀላል ነው:: ውጫዊ ነገሮች የሚለወጡ በመሆናቸው በእለት ልዩነት ምርጫዎቻችን የሚለዋወጡ መሆናቸው ግድ ነው:: ቀኑን ሙሉ አንዱን ስንመርጥ ሌላውን ስንጥል እንውልና በንጋታውም አዲስ ምርጫ ለማድረግ እንዘጋጃለን: : ይህ አይነቱ የለት ኑሮ ሰውን በምድር እረፍት የለሽ አድርጎታል:: የተረጋጋ እና የሰከነ ህይወት የህልም ያኽል ርቆታል:: እኔ ግን አሁንም እያልኩ ያለሁት 'ከዚህ እረፍት አልባ ህይወት የምንወጣው ምርጫዎቻችንን በማስተካከል እንኳ አይደለም ፤ ከነ ጭራሹ መምረጥን ስንተው ነው' ነው እያልኩ ያለሁት::

ምርጫ ማድረግ ዋጋ የሚኖረው ከማህበረሰቡ አንፃር ብቻ ነው:: ከግለሰቡ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለውም:: በተፈጥሮ ደሞ እውን የሆነው ግልሰቡ ነው: : ማህበረሰቡ የሚፈጠረው ግለሰቡ በሚይዘው የህይወት ግንዛቤ ላይ ተመስርቶ ነው:: ግለሰቡ ደሞ የህይወት ግንዛቤው በመረዳቱመጠን የሚወሰን ስለሆነ በተፈጥሮ ከተገኘው ግለሰብ ይልቅ ማህበረሰቡ ትክክል የመሆን ውስንነት ያለበት ነው:: ምርጫ ማድረግ ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማህበራዊ ዋጋ ሊሰጣቸው የሚችሉ ነገሮችን ብቻ ነው የሚመለከተው:: እነዚህ ሁሉ እውነታዎች ሲሰበሰቡ አንድ ግልፅ የሆነ ማጠቃለያ ይሰጣሉ::

እሱም :- ምርጫ የሚደረገው በአእምሮ በኩል ነው: : አሁን ሰዎች የያዙት አእምሮ በማህበረሰቡ ባህል እና ወግ እንዲሁም ማህበረሰባቸው እውቅና በሰጣቸው እውነታዎች የተሞላ ነው:: ከላይ እንዳነሳሁት ማህበረሰቡ ደሞ የትክክለኝነት ወሰን አለበት:: ይህም በመሆኑ ሰው ሲመርጥ የሚመርጠው ተፈጥሯዊ የሆነውን ግለሰብ ጥያቄ ለመመለስ ሳይሆን ማህበረሰባዊ የሆነውን ጥያቄ ለመመለስ መሆኑ በጣም ግልፅ ነው:: ይህ ደሞ በውስንነት ያለ በመሆኑ ከወሰን አልባው ዩኒቨርስ ጋር የተቃረነ ነው:: ከራሳችን ህልውና ጋር ተቃርነን በጭራሽ ደስተኝነት ሊከሰት አይችልም:: ለዚህም ነው መምረጥ ከንቱ የሆነ የሰዎች ድርጊት ነው ያልኩት::

ታዲያ ልብ በሉ አለመምረጥ ማለት ወደ ውስጥ አለማተኮር ማለት አይደለም:: ሰው ውስጡን ሊመርጥ ይገባል:: ውስጣችን ከውጪያችን በተሻለ ብቻ ሳይሆን ሙሉለሙሉ ተፈጥሯዊ ነው:: ከውጭ ለማህበረሰቡ ብለን ልንዋሽ እና ልናስመስል እንችላለን:: ከውስጥ ግን ሁሌም ለራሳችን ታማኝ ነን:: መቼም ቢሆን ውስጣችንን ልንዋሸው አንችልም:: ብቻችንን ሆነን ከራሳችን ጋር ብቻ በቀረንባቸው ጊዜያት እውነተኛው ማንነታችን ብቅ ይላል:: ያ ለማህበረሰቡ ተብሎ የተደበቀው ንፁህ ማንነት ወደ መኖር ይመጣል:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ብቻ ስንሆን ነው ውጫዊ ነገሮችን ማሳደድ እና ህይወትን በውጫዊ ነገሮች ላይ መመስረት ትክክል እንዳልሆነ ግልፅ የሚሆንልን::

አእምሯችንን ተከትለን የምንመርጠው ነገር ሁሉ ከስግብግብነት እና ከበላይነት ፍላጎት የመነጨ ነው:: ምክንያቱም በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ማግኘት እና መከበር እንፈልጋለን:: ማህበረሰቡ የሆነ አይነት ሰው ካልሆንን በቀር በአክብሮት ስለማይቀበለን እና ዋጋ ያጣን ስለምንሆን የውጫዊ ምርጫዎች መነሻ ጥሩ ያልሆነ ስነ ባህሪ ነው ማለት እንችላለን::

ስግብግብነትም ሆነ የበላይነት ፍላጎት ከዮኒቨርስ ባህሪ ጋር ፈፅሞ የሚቃረን ነው:: በህልውና ግንዛቤ ሁሉም ያለው እኩሉን ነው:: ትንሽ ያልነው ያለው፤ ትልቅ ያልነው ያለውን ነው:: ትልቅ ያልነውም እንደዛው: : ሁሉም ነገር በአንድ የተዋሀደ ነው:: በዚህ ውህደት ውስጥ መበላለጥ ሊከሰት ፈፅሞ አይችልም:: ማንም የበላይ ማንም የበታች አይደለም:: የባህሪ መወራረስ እስካለ ድረስ እኔ ያለኝ አንተም አለህ:: አንተ በኔ ልትቀና የምትችልበት ምክንያት አይኖርህም:: በቃ ሁላችንም እኩል ነው ያለን:: መስገብገብም ሆነ የበላይነት ፍላጎት ሊኖረን አይገባም:: የበላይነት እና የስግብግብነት ስሜት ካለህ ግን መምረጥ ውስጥ ነህና በህይወት ደስተኝነት ሊከሰትልህ አይችልም::

በመጨረሻም አንድ ግንጥል ታሪክ አካፍያችሁ ላብቃ:: ሰውዬው በጣም የተማረ ነው:: ግን አሁንም የሚያረካውን ፍለጋ በመዞር ላይ ነው:: የሚያረካኝን አገኛለሁ ብሎ የሚያስበው ያለውን 'ሀብት'ያለውን ጭንቅላቱን በመሸጥነው:: ለዚህም ደሞ በየገበያው ቦታ ሲዞር ይውላል:: በዙረቱ መጨረሻ ላይ ግን አደን ዝም ብለው የተቀመጡ ሰውዬ ጋር ይገናኛል:: ሰውዬውንም ጭንቅላት ይገዙ እንደሆነ በመጠየቅ ይቀርባቸዋል:: የዚህን ጭንቅላት ሻጭ ብኩን ሰው ሁኔታ የተረዱት ሰውዬው እንዲህ ሲሉ መከሩት:: ቅንጭብ ታሪኩ :-

ስመጥር ከሆኑ ዮኒቨርስቲዎች ኮሌጆች በምሰራበት ወቅት ያዳበርኩትን ፤ ያነበብኩትን ያወቅኩትን እውቀት ልሸጥ ብወጣ <ሻጭ> መሰልኳቸው እና ያማርጡኛል: : እንዳው እንዲህስ መንከራተት ነበረብኝ?.. አይ የሰው ልጅ እንዲህ ለእውቀት ግድ የለሽ ይሁን? ደግሞ ይህንን የመሰለ እውቀት ተሸክሜ እደጃፋቸው እየሄድኩ <ግዙኝ> ብሎ መጠየቅ ያሳፍራል ፤ እንደርካሽ ነገር < ግዙኝ እባካቹህ>ልል ፤ ግን ደግሞ ሳልሸጥ ብመለስ እንዴት ሊኖር ነው:: መሸጥ አለብኝ :: ለስሜም ለሆዴም ይጠቅመኛል::

ይህንን እያውጠነጠንኩ አንድ ብቻውን ሆኖ በዝምታ የተቀመጠ ሰው አየሁ " እድለኛ ነኝ በእውነት እድለኛ ነኝ ሸጥኩት በቃ!"ሰውየውን ቀረብኩት እና ፤" ጌታዬ ?" አልኩት :: በውስጤ ብናደድም <እኔ አንተን ጌታዬ> ይገርማል ብቻ:: ካጎነበሰበት ቀና ብሎ ፤" አቤት? "አለኝ በተረጋጋ ድምፅ :: ፤" እ...ጭንቅላት ትገዛለህ ?" አልኩት በኩራት:: አሁን ደስ አለኝ እኔ ጭንቅላት ሻጭ እሱ ደሞ ገዥ :: ያለማቅማማት ይስማማል ብዬ አስባለሁ ፤ ሲያዩት የተማረ አይመስልም ራሱን የሌለ ጥሎታል::

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የሥራ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ቀጥሎ ባሉት የስራ መደቦች አመልካቾችን አወዳድሮ በቅጥር ለሟሟላት ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት መስፈርቱን የምታሟሉ አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 (አምስት) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስረጃችሁን ዋናውን እና የማይመለስ ኮፒ በመያዝ ከታች በተገለፀው ቀን እና ቦታ እየቀረባችሁ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ማሳሰቢያ

- የቅጥር ሁኔታ በቋሚነት፡፡
- ክፍት የስራ መደቡ የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟሉ፡፡
- ለማንኛውም ዓይነት ፈተና ማለፊያ 60% (ስልሳ ከመቶ) ይሆናል፡፡
- የስራ ልምዱ ህጋዊ ግብር የተገበረበት መሆን አለበት፡፡
- የዕዳ ማጣሪያ (ክሊራንስ) ማቅረብ የሚችሉ፡፡
- ከግል ተቋም የሚመጣ የስራ ልምድ ተቀባይነት የሚኖረው የሥራ ግብር የተከፈለበት ማስረጃ ማቅረብ ሲቻል ብቻ ነው፡፡
- ለመመዝገብ ሲመጡ ኦርጂናል ዶክመንት እና የማይመለስ ኮፒ መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ከመንግስት ዩኒቨርሲቲ ለውድድር የሚመጡ ዕጩ ተወዳደሪዎች የወጪ መጋራት የጨረሱበት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
- ከዩኒቨርሲቲ ወይም ከኮሌጅ የት/ት ማስረጃቸውን ትክክለኛነት/Authentication/ ያረጋገጡ።
- በቂ ዋስትና ማቅረብ የሚችሉ፡፡

**የመመዝገቢያ ቢሮ**

**ድሬደዋ ደወሌ የክፍያ መንገድ ላሰደሬ የክፍያ ጣቢያ**

**0912952050**

**አድራሻ፡-በሸገር ከተማ የኮዬ ፈጬ ክ/ከ አስተዳደር ቱሉ ዲምቱ ወረዳ**

**ቱሉ ዲምቱ ዋና የክፍያ ጣቢያ**

**ስልክ ቁጥር 0114-17171**

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ደረጃ | ብዛት | የትምህርት ዝግጅት | የስራ ልምድ | ልዩ ችሎታ | ደመወዝ | የስራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ የሰው ኃብት እና ፋሲሊቲ ባለሙያ | XII (12) | 1 | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት፣ በህዝብ አስተዳደር፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን፣ በሰው ኃብት አስተዳደር ወይም በተመሳሳይ የት/ት መስከ ሁለተኛ ዲግሪ/ማስተርስ/ | 2 ዓመት አግባብ ያለው የስራ ልምድ | | 14,816 | ድሬደዋ ደወሌ(ከላስዴሬ የክፍያ ጣቢያ እስከ ደወሌ) |
| | | | | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት ፣ በህዝብ አስተዳደር ፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ፣ በሰው ኃብት አስተዳደር ወይም በተመሳሳይ የት/ት መስከ የመጀመሪያ ዲግሪ | 4 ዓመት አግባብ ያለው የስራ ልምድ | | | |
| 2 | ከፍተኛ የሕግና ኢንሹራንስ ባለሙያ | XII (12) | 1 | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በሕግ የተመረቀ ሁለተኛ ዲግሪ/ማስተርስ/ | 2 ዓመት አግባብ ያለው የስራ ልምድ | | 14,816 | ድሬደዋ ደወሌ(ከላስዴሬ የክፍያ ጣቢያ እስከ ደወሌ) |
| | | | | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በሕግ የተመረቀ የመጀመሪያ ዲግሪ | 4 ዓመት አግባብ ያለው የስራ ልምድ | | | |
| 3 | ከፍተኛ የትራፊክ ደህንነት ባለሙያ | XII (12) | 1 | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢንጂነሪንግ፣ በሲቪል ኢንጂነሪንግ፣በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት፣ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት የት/ት መስከ ሁለተኛ ዲግሪ/ማስተርስ/ | 2 ዓመት አግባብ ያለዉ የስራ ልምድ | | 14,816 | ድሬደዋ ደወሌ(ከላስዴሬ የክፍያ ጣቢያ እስከ ደወሌ) |
| | | | | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢንጂነሪንግ፣ በሲቪል ኢንጂነሪንግ፣በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት፣ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት የት/ት መስከ የመጀመሪያ ዲግሪ | 4 ዓመት አግባብ ያለዉ የስራ ልምድ | | | |

## < < ጀሶ . . .

ከገጽ 6 የዞረ

የሌሎች አገሮች ተሞክሮ፡- በዚህ ነጥብ ላይ የሌሎች አገሮች ሕጎች ምን ይመስላሉ? የሚለውን ስንመለከት፣ ከአገራችን የምግብ መድኃኒትና ጤና አጠባበቅ አዋጅ ጋር አቻ የሆነው የማሌዥያ የምግብ ሕግ ግልጽ ትርጉም የሰጠ ሲሆን፣ ይኸውም ምግብ ከባዕድ ነገር ጋር ተደባልቋል የሚባለው የምግቡን የምግብነት ደረጃ ሊያወርዱ የሚችሉ ወይም በየትኛውም ሁኔታ ከነባሩ የምግብነት ደረጃ አንፃር ዝቅ ያለ የንጥረ ምግብ ይዞታ እንዲኖረው የሚያደርግ ከሆነ፣ ምግቡ ከባዕድ ነገር ጋር ተደባልቋል ሊያስብል እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

የሲንጋፖር የምግብ ሕግ ደግሞ ምግብ ከባዕድ ነገር ጋር ተደባልቋል የሚባለው የምግብነት ይዘቱን የሚቀንሱ ንጥረ ነገሮች መጨመር ወይም መደባለቅ ብቻ ሳይሆን በምግቡ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸውን አንዳንድ ይዘቶችና ንጥረ ነገሮችን አለማካተት ጭምር በትርጉም ተካቶ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የአገራችን ሕጎችም ከዚህ አንፃር የሚታይባቸውን ክፍተት ቢያርሙ ሕግን በማስፈጸም ሒደት ውስጥ እየተከሰተ ያለውን የመናበብ ችግር ሊፈታ ይችላል፡፡

ተግባራዊ ተግዳሮቶች፡- የአገራችን ሕግ ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር መደባለቅን በተመለከተ ምንም እንኳን ጉዳዩን በልዩ ሁኔታ እንዲመለከት ታስቦ የወጣው አዲሱ የምግብ መድኃኒትና ጤና አጠባበቅ አዋጅ በጉዳዩ ላይ ዝምታን ቢመርጥም የሸማቾች ጥበቃ አዋጅና የኢፌዴሪ ወንጀል ሕግ ከነጉድለታቸው የሕግ አተረጓጎም መርሆዎችን ተከትሎ በጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛል፡፡ ከዚው ጋር በተያያዘ ክፍል ሁለት ይቀጥላል፡፡

## የተቋማት . . .

ከገጽ 1 የዞረ

በቢሮ ደረጃ የችግሩን ስፋት ለመለየት እና የመፍትሄ አቅጣጫ ለማመላከት በተመረጡ ተቋማት ጥናት መካሄዱን ጠቁመዋል፡፡ በቀጣይም የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ የትግበራ ስትራቴጂ መዘጋጀቱን እና በቀጣይም በስትራቴጂው መሰረት ተቋማቱ ያሉባቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች በአግባቡ ለመፍታት በሙሉ አቅማቸው ልዩ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩና ለውጤታማነቱም እንደተቋም አስፈላጊውን ክትትል እና ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑን ተናግረዋል። ሲል የዘገበው የተቋሙ ህዝብ ግንኙነት ክፍል ነው፡፡

## በኢትዮጲያ . . .

ከገጽ 12 የዞረ

ከጨዋታው መጠናቀቅ በኋላ አስተያየት መስጠት የቻሉት የድሬዳዋ አሰልጣኝ አስራት አባተ "የተጋጣሚ ቡድን በልምድም ባለው ኳሊቲም የተሻለ አቅም እንዳለው እናውቃለን ፤ሆኖም ሚዛናዊ የሆነ አጨዋወትን ለመጫወት ነው ይዘን የገባነው የተደራጀን ሆነን ለመጫወት ሞክረናል፤ ግን ከዕረፍት በፊት ወደ ፊት መሄድ አልቻልንም፡፡ ያንን የመለወጥ ዕሳቤ ይዘን ነው ከዕረፍት በኋላ የገባነው በተወሰነ መልኩም በአጨዋወታችን ትንሽ ለውጥ ነበረን ፡፡ በተደጋጋሚ በሰራንበት ፣ በፈራነው ሁኔታ ላይ ተደጋጋሚ የቅጣት ምት ዕድሎችን ተጋጣሚ ቡድን አግኝቶ ነበር እና ያንን ዕድል እስኪያገኝ ድረስ ጥሩ ለመንቀሳቀስ ሞክረን ነበር፡ ፡ ከጎሉ በኋላ ግን በተወሰነ መልኩ ክፍተት ነበረብን" ሲሉ ሀሳባቸውን ገልፀዋል።

## በአራቱ. . .

ከገጽ 1 የዞረ

የተመረቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ረገድ በተለይም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተሰሩ ስራዎች አመርቂ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

የተመረቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ህብረተሰቡ እንዲጠብቀው እና እንዲከባከብ በማድረግ በኩል ሰፊ ስራዎች መከናወናቸውንም ነው ሀላፊው ያነሱት፡፡

የብልጽግና ፓርቲ ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሀላፊ ክቡር አቶ ኢብራሂም ይሱፍም በበኩላቸው ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ህዝቡ ሲጠይቃቸው የነበሩ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመመለስ ከተደረጉት ጥረቶች መካከል ሰሞኑን የተመረቁ የልማት ፕሮጀክቶች መሆናቸውን ተናግረዋል፡ ፡ በቀጣይም የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል በትኩረት እንደሚሰራም ነው የገለፁት፡፡

**በሰላም ለማ**

# ገናን በድሬዳዋ

በፋንታዬ ዳንሴ

ሰሞኑን የገና በአል ነበር ከዋዜማው አንስቶ እስከ በአል ቀኑ ደመቅ ደመቅመቅ ብሎ ዘመድን ከዘመድ ጓደኛን ከጓደኛ አገናኝቶ ያለፈው ገና የፍቅር ተምሳሌት በሆነችው በድሬዳዋ ምን ይመስል ነበር ለምንል ሰዎች በሙሉ ከዋዜማው ጀምሮ በድሬ በአል ይህን ይመስል ነበር ስንል ልናስቃኛችሁ ወደድን፡፡

እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲሁም ጤዛ ነሽ! እንዳለው የሐገሬ ሰው እንኳን በአል ሆኖ ዘመድን ከዘመድ ወዳጅን ከወዳጅ የሩቁን ከቅርብ የሚያገናኝ የፍቅር ቀን ይቅርና የፍቅር ሐገር የሆነችው ድሬማ እንዴታ?? (በእርግጥ ይህንን አባባል በብዛት የምንጠቀመው በአሉታዊ ጎኑ ቢሆንም) ከዋዜማው አንስቶ ይሕን በማሳየት የፍቅር ከተማ መሆንዋን አስመሰከራለች፡፡

ከተማዋን ዞር ዞር ብሎ ለቃኘ አሸዋ፣ቀፊራ፣ሰኢዶ፣ኮኔል ወዘተ... በበአሉ ድባብ አሸብርቀዋል፤ የሰላም ጨኸት ከየቦታው ያስተጋባው አቤት ውብ አቤት ድምቀት ከሩቅ ሐገር መጥቶ ላየ ሰው የድሬ ጨኸት እና ትርምስምስ ሳያስደንቀው የሚቀር አይመስለኝም፡፡

ዞር ዞር ብሎ ላየ አስደሳች አዝናኝ እና አስተማሪ ክስተቶች በአሉን ተከትሎ በውቧ ድሬ ብቅ ብቅ ሳይሉም አልቀረም፡፡ በየመንገዱ ያሉ ፊልም ቤቶች፣መዝሙር ቤቶች፣ሙዚቃ ቤቶችን ጨምሮ በገና መዝሙሮች የአላፊ አግዳሚውን ጆሮ ይስባሉ፡፡ በየስጦታው መሸጫ የገና ዛፍ፣ ፖስት ካርድ፣ የተለያዩ የገና ስጦታዎች የቤት ማስዋቢያ እቃዎች ሞልተዋል። አንዱ ለፍቅረኛው ሌላው ለጓደኛው ሌላውም ለቤተሰቡ ብቻ ሁሉም በየፊናው የስጦታውን አይነት ያሸጎደጉደዋል ሻጩ ራሱ ይሕን ሁሉ ሰው ማስተናገድ ስለማይችል አንዳንዶች ሰሚ አጥተው ትተው የወጡም አሉ። ገና ገና(ላልቶ) ይነበባል ምኑ ተነካና አሸዋ ቀፊራ ሰኢዶ መተላለፊያ መንገድም የለም ጠጠር መጣያም አይገኝም።

የድሬዳዋ ዋና የገበያ ማዕከል የሆነው እንኳን በድሬዳዋ ነዋሪ በሌላውም የሚታወቀዉ አሸዋ ገበያ አይደለም በአል ሆኖ ይቅርና ሌላም ጊዜ ያለው መጨናነቅ ድንቅ ነው ሰሞኑን ከወትሮው ለየት ባለ መልኩ መንገድ ተጨናንቋል ፣ ገበያተኛ በዝቷል ጠጠር መጣያም የለም፤ መገፋፋቱ መጣበቡ ለየት ያለ ነው፡፡ ሰው ከሰው፣ከእንስሳ ከተሽከርካሪ ይጋጫል፡፡ ሕዝቡ ልብስ፣ጫማ ፣ደርዘን ተራ እያለ ሲተረማመስ ላየ ሰው እንኳን አሸዋ ገበያ ይቅርና ከዚህ በፊት ሱቅ መጥቶ የሚያውቅ አይመስልም፡፡ የጸሐይ ሙቀቱ የማይበግረው ይህ ሕዝብ ሁሉን ችሎ በአልን ሊያከብር ደመቅ ሸብረቅ ለማለት ልጆቹን ቤቱን ለማሳመር እየተሯሯጠ ይገኛል። ሻጮችም ከወትሮው ለየት ባለ መልኩ የሕዝቡን ብዛት ለመቋቋም ይሯሯጣሉ ገበያም ሲበዛ ደግሞ በዚያው ዋጋም ያስወድዳል ድሮ ለምኖ ተማጽኖ የሚሸጠው ነጋዴ ሁሉ ዛሬ ኩራቱ ሰማይ ደርሷል ማን ይደርስበት ይሆን

ከዚያ ራቅ ሳይል ሌላው አይነት አይነቱን ሽቶ ያማርጣል ሌላው ለሚስቱ ለልጁ ለፍቅረኛው ብቻ ለራሱም ያማርጣል ከዚያ መንደር ላለፈ መአዛው ይማርካል ድሬ እነደሆን በሽቶ አትታማም በቃ ሕዝቡም ይገዛል።

ዞር ብሎ ለሚያይ ሰው የባንክ ቤቱ ሰልፍ አቢሲኒያ፣ንግድ፣ አዋሽ ሌላው መተላለፊያም የለም ተማሪዎችን ጨምሮ አንዳንዱ ብዙ ጊዜ ያጠራቀመውን ይዞ ሚወጣ ነው ሚመስለው የብሩ ብዛት ሌላው ከተለያየ ቦታ የተላከለትን ያወጣል፣ ሌላው ያስቀመጠውን ፣ተማሪዉ ቤተሰብ ለበኣል መዋያ የላከለትን ያወጣል ሌላው ከውጭ ሐገር የተላከለትን ይመነዝራል በቃ ሁሉም በየፊናው ሩጫ ላይ ነው።

ባጃጁም ፎርሱም ይርመሰመሳል፡፡ ቀፊራ ይላል አንዱ ሁሉም ገባ ቀፊራ ደግሞ ሌላው ገበያ ነው ሁሉም የሚያስፈልገውን ይገዛል ገበያው ተጨናንቋል።

ያው በአል ከተነሳ አይቀር የኑሮ ውድነትም አብሮ መነሳቱ አይቀርም የእናቶች የጤፍ ምርጫ ዋጋ ምንም ቢወደድም ተወደደና ሳይበላ አይታደር ያማርጡታል፡፡ ነጭ ጤፍ፣ ቀይ ጤፍ፣ ስንዴ ለዳቦ፣ የበቆሎ ዱቄትን ለአብሲት ይገዛሉ ክብር ለእናቶች የቤተሰቡን ክፍተት ለመሙላት የሚያደርጉት ጥረት ይመሰገናል። አባቶችም



በየፊናቸው የፍየል፣የበሬ ዋጋ ይጠይቃሉ ሌላው ዶሮ ይገዛል ሁሉም እንዳቅሙ ከወዳጅ ዘመዱ ጋር በአልን ሊያከብር ቤተሰብን ለማስደሰት ሩጫ ላይ ነው የገበያው ድባብ ለየት ማለቱ ከሩቅ ሆኖ ለሚያይ ሰውም የተሰወረ አይደለም።

እንግዲህ ሁሉም በቤቱ ሆኖ አባ ወራ ያርዳል ፣እናቶችና ልጆች የታረደውን ይበልታሉ ሌላው ሽንኩርት ይከትፋል ጠላ፣ኬኔቶ፣ ብርዙ ሁሉም አለ ዳቦ ይደፋል ቤት ይስተካከላል። በበአሉ ቀን ጎረቤት ይጠራል፣ ወዳጅ ዘመድ ይሰበሰባል ፣ከሩቅ ከቅርብ ይጠራራል ፣ችግረኛ ሀብታም ደሀ ማለት የለም ሁሉም ይሰበሰባል እናም በድሬ በአንድነት በአሉ ተከበሮ ዋለ፡፡ ከተማው በበአል ቀኑ ድባባ አሸብርቆ ትልቅ ትንሹ አምሮበት አልፏል፡፡

የእንኳን አደረሳቹ መልዕክት ከየቦታው ለወዳጅ ዘመድ ይላካል ሆቴሎች ሁሉ ደምቀዋል። እንኳን ለጌታችን ለመድሐኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የገና በአል አደረሳችሁ በአሉ የሰላም የፍቅር የአንድነት የመያያዝ ድሆችን ምናስብበት በአል ይሁንልን እያልን በሰሞነኛ በድሬዳዋ የነበረውን የበአል ድባብ እንዲህ ባለ መልኩ ለመቃኘት ሞክረናል፡፡

የጌታችን መወለድ ስናስብ እና ስናከብር በተገቢው መንገድ መሆን አለበት ያሉት ብጹዕ አቡነ ናትናኤል እንደገለፁት በአሉን በተገቢው መንገድ ማክበር አስፈላጊ እንደሆነም ገልጸዉ ነበር ፡፡ ባለፉት ጊዜያት ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘነው ከንግግሩ ጥቂት እነሆ ፡-

" ... ይህንን የልደት በዓል ስናከበር የት ነው የምንሄደው ? ቀድሞ በዓሉን ለማክበር የት ነው የምንሄደው ? ስንል ጭፈራ ቤት አይደለም፣ ሙዚቃ ቤት አይደለም ፣ ይሄ በዓል የሚከበረው በጭፈራም አይደለም፤ በዘፈንም አይደለም፣ በሙዚቃም አይደለም፤ በበዓላችን ላይ ሙዚቃ እየቀላቀላችሁ ጭፍራ እያስገባችሁ የበዓሉን እሴት ሃይማኖታዊ ትርጉም የምታበላሹት የሚዲያ አካላት ናችሁ።

ይሄ በዓል የሚከበረው በጭፈራም አይደለም፤ በዘፈንም አይደለም፤ በሙዚቃም አይደለም። የበዓሉን ትርጓሜውን ማወቅ ያስፈልጋል። ያን እለት መላእክትና ሰዎች አልዘፈኑም እኮ፣ አልጨፈሩም እኮ ፤ መላእክትና ሰዎች ደስታቸውን የገለጡት በምስጋና ነው። ዕለቱ የሚከበረው በምስጋና ነው። አባቶቻችን የበዓሉን አከባበር ወደኛ ያደረሱት በዚህ መንገድ ነው። እኛም ለትውልድ የምናስተላልፈው በዚህ ሁኔታ ነው።

የበዓሉን መንፈሳዊ ስነስርዓት በጠበቀ መልኩ ወደትውልድ ማስተላለፍ ይኖርብናል። የበዓሉንም መንፈሳዊ ስነስርዓት እሴት ስንል ለምን ተወለደ ? የት ተወለደ ? ከሚለው ትርጓሜ ይጀምራል፤ ሲወለድ ምን ተከሰተ፣ ምን ተደረገ ? መላዕክት፣ እረኞች፣ ሰባሰገል ምን አደረጉ ? ድንግል ማርያም ምን አደረገች ? እንስሳትስ ምን አደረጉ ? የሚሉትን ነገሮች ነው የምንወስደውና የምናስበው። ስለዚህ እነሱ ያደረጉትን እያደረግን ነው ለትውልድ ማስተላለፍ የሚገባን።

ይህ ለልደት በዓል ብቻ ሳይሆን የጥምቀት በዓልም፣ ሌሎች መንፈሳዊያን በዓላቶቻችን ሁሉ መንፈሳዊያን





በዓላት እስከሆኑ ድረስ በመንፈሳዊ ስነስርዓት ነው ማክበር የሚገባን፣ ሃይማኖታዊ በዓል ብለን እስከሰየምን ድረስ ሃይማኖቱ በሚፈቅደው ስነስርዓት/እሴት ነው በዓላቱ ተከብረው መዋል ያለባቸው፤ ተከብረው ማለፍ ያለባቸው። ትውልዱም ማወቅ እና መማር ያለበት በእንዲህ ያለ ሁኔታ ነው። በማለት እጅግ ጠቃሚ ሐሳብ አንስተዋል የበአሉ ድባብ ሙሉ ለሙሉ ባይቀየርም ግን መልእክቱ በብዙዎች ዘንድ ጥሩ ተጽእኖ ፈጥሯል ይህንንም በጥቂቱ ለማየት ችለናል፡፡

እሑድን የከተማዋን ድባብ ወጣ ብሎ ላየ በአል በድሬዳዋ ምን ያህል ደስ የሚል እነደሆነ ለመግለጽ ቃል ያጥራል የከተማው ውበት፣ የሕዝቡ የአለባበስ ድምቀት፣ የሆቴሎች ሳቢነት፣ የሙዚቃው ድባብ፣ የቤተክርስቲያናቱ አምልኮ፣ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች በከተማዋ ላይ መብዛት ለከተማው የሰጠው ጥሩ ገጽታ ፣ ከፍቅረኛው፣ ከቤተሰቡ ጋር አምሮበት ደምቆ በአልን ሊያከብር የወጣ ሕዝብ የከተማውን ድባብ ቀይሮታል እጅግ ይማርካል።

የፍቅር ሐገር በሆነች ድሬዳዋ ሙስሊም፣ ኦርቶዶክስ፣ ፕሮቴስታንት ሌሎችን ጨምሮ በሐይማኖት መከፋፈል ሳይኖር ሁሉም ከወዳጅ ዘመድዎ፣ ከጎረቤት ጋር ተጠራርቶ በአልን በፍቅር ያከብራል። ከጠዋቱ ጀምሮ እስከ ምሽቱ ድረስ አምሮ ደምቆ የተከበረው የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ በድሬዳዋ በሚያስደምም መልኩ ተከብሮአል፡፡

**እንኳን አደረሳችሁ አደረሰን!!**

## የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ፖሊስ አካዳሚ በራሱ አቅም ያሰለጠናቸውን መካከለኛ አመራሮች አስመረቀ

- በመርሐ ግብሩ ላይ የቆይታ ግዜያቸውን ያጠናቀቁና በስራ አፈጻጸማቸው ላቅ ያሉ አመራር እና አባላት የማዕረግ ዕድገት ተሰጥቷቸዋል ።

በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የፖሊስ አካዳሚ ስልጠናቸውን ሲከታተሉ የቆዩ መካከለኛ አመራር ፖሊሶች እና የቆይታ ግዜያቸውን ያጠናቀቁ እና በስራ አፈጻጸማቸው ላቅ ያሉ አመራር እና አባላት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሃር ፣ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ዋና አዛዥ ክቡር ኮሚሽነር አለሙ መግራ የካቢኔ አባላትና የድሬዳዋ ፖሊስ ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ተመርቀዋል፡፡

የእለቱ የክብር እንግዳ የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሃር በምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ በመገኘት ባስተላለፉት መልዕክት ለበርካታ አመታት መላው ኢትዮጵያውያን ሲቆጩበት የነበረውን እና በክቡር የሀገራችን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ በሳል አመራር ሰጪነት ሀገራችን ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት በሆነችበት ወቅት እንዲሁም በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አካዳሚ የእጩ መኮንንነት ስልጠና አጠናቃችሁ ለዛሬዋ የማእረግ ቀን የበቃችሁ እንዲሁም የቆይታ ግዜያችሁን በላቀ የስራ አፈጻጸም አጠናቃችሁ ወደ ቀጣይ የማእረግ እርከን የተሸጋገራችሁ አመራር እና አባላት በዚህ ታሪካዊ በሆነ ቀን ማእረግ በማግኘታችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል።



የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የድሬዳዋን ሰላም እና ጸጥታ አስተማማኝ ለማድረግ በተከናወኑት ዘርፈ ብዙ ስራዎች ተቋሙ አመርቂ ውጤት እያስመዘገበ ነው ያሉት ክቡር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ እያስመዘገበ ያለውን አንፀባራቂ ውጤት በዘላቂነት ለማረጋገጥ የእለቱ የማእረግ ማልበስ ስነስርአት አይነተኛ ፋይዳ እንዳለው ጨምረው ተናግረዋል ።

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ለውጡን ተከትሎ ከሰራቸው ደማቅ ሰራዎች ተቋሙን በሰው ሃይል ስልጠና ማደራጀት አንዱ ነው ያሉት የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ኮሚሽነር አለሙ መግራ ማእረግ የማልበስ ስነ-ስርአቱም የዚህ ስራ ውጤት አንዱ አካል በመሆኑ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ እራሱን በሰው ሃይል ለማደራጀት መሰረት የተጣለበት ታሪካዊ ቀን ነው ማለት ይቻላል ብለዋል።

ክቡር ኮሚሽነሩ አክለውም የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በሰራቸው ሰፋፊ ስራዎች አንዱ የእጩ መኮንንነት ስልጠና በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ፖሊስ አካዳሚ ስልጠናችሁን አጠናቃችሁ ለዛሬዋ የማእረግ ቀን የበቃችሁ እንዲሁም በስራ አፈጻጸም እና ባስመዘገባችሁት ላቅ ያለ ውጤት ወደ ቀጣይ የማእረግ እርከን የተሸጋገራችሁ አመራር እና አባላት በዚህ ታሪካዊ በሆነ ቀን ማእረግ በማግኘታችሁ እንኳን ደስ አላችሁ በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል ።

በመርሀ ግብሩ ላይ የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ም/ፕሬዘዳንት ም/ኮሚሽነር ዳንኤል ብርሀኑ ለተመራቂዎቹ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን 76 የሆኑ መካከለኛ አመራር ተመራቂዎች እንዲሁም 146 ለሆኑ የቆይታ ግዜያቸውን ያጠናቀቁ እና በስራ አፈጻጸማቸው ላቅ ያሉ አመራር እና አባላት ማእረግ የማልበስ እና በትምህርታቸው ብልጫ ላመጡ አባላት እንዲሁም ስልጠናው እንዲሳካ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ተቋማት እና ግለሰቦች ከእለቱ የክብር እንግዶች ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

## "ትላንት ሀገርን ጠብቀው ያስረከቡንን አረጋዊያንን መጠበቅና መንከባከብ ግዴታችን ነው"

ኮማንደር ትእግስት ተሾመ
በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ
የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር



የገና በአልን አስመልክቶ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ከወጣት የማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀት ጋር በጋራ በመሆን በመቆዶንያ የአረጋውያን እና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማእከል በመገኘት የተለያዩ የበጎነት ተግባራትን አከናወኑ።

በዚሁ ፕሮግራም ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ኮማንደር ትእግስት ተሾመ እንደገለጹት አረጋዊያንን መርዳትና መንከባከብ በሰብአዊነት የማገልገል አንዱ ድርሻ ሲሆን እኛ ፖሊሶች ደግሞ ትላንት ሀገርን ጠብቀው ላስረከቡን ዛሬ ግን በተለያዩ ምክንያቶች ጧሪ ያጡትን እና የጤና እክል ያጋጠማቸውን አረጋውያንን መደገፍ ግዴታችን ሲሆን ዛሬ የምንሰራው መልካም ስራ ነገ መልሶ ይከፍለናልና ሁላችንም አረጋዊያንን ልንደግፋቸው ይገባል ብለዋል።

በዚሁ በጎ ተግባር ላይ ለመሳተፍ የተገኙት በማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ምክር ቤት አባል ወ/ሮ ኢፍቱ አባስ በበኩላቸው አረጋዊያን እና የአእምሮ ህመም ያለባቸው ሰዎችን መርዳት የሁላችንም ሀላፊነት ሊሆን ይገባል፡፡ ዛሬ እዚህ የምናያቸው ሰዎች ትላንት ትልቅ ቦታ የነበሩ ፤በራሳቸው መንቀሳቀስ የሚችሉ ፤ሰዎችን የሚረዱ፤ ሀገርን በብዙ ዘርፍ ያገለገሉ፤ ሲሆን ዛሬ ላይ ግን በተለያየ ምክንያት እዚህ ደረጃ ላይ ሊደርሱ ችለዋል፤ እኛም ነገ ምን ሊደርስብን እንደሚችል ስለማናውቅ መልካም ነገር ማድረግ ደግሞ መልሶ ስለሚከፈል ሁላችንም በመልካምነት አቅመ ደካሞችን ልናግዝ እና ልንደግፍ እንደሚገባ ገልፀዋል።

በመቆዶኒያ የአረጋውያን እና የአእምሮ ህሙማን መረጃ ማእከል በመገኘት አንድ መቶ ሀምሳ ለሚሆነ አረጋውያን የቁርስ መመገብ ስነ-ስርአት እንዲሁም ፀጉራቸውን መቁረጥ እግራቸውን ማጠብ ስራን የድሬዳዋ ፖሊስ ማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት አባላትና የወጣት አደረጃጀት በጎ ፍቃደኞች በጋራ በመሆን ያከናወኑ ሲሆን የፕሮግራሙ መጨረሻም የአረጋውያኑ ምርቃት ሆኗል።

## የቱሪዝም ዘርፋችንን ለማሳደግ በቴክኖሎጂ በመደገፍ የከተማችንን ሰላም የማስጠበቅ ስራ መስራት እንደሚገባ ተገለጸ



ይህ የተገለጸው የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር‹‹ ድሬ የተቀናጀ የእንግዶች መርጃ አስተዳደር›› ሲስተም የማስጀመሪያ የውይይት ፕሮግራም በተካሄደበት ወቅት ነው፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ በመገኘት የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ ኃላፊ ምክትል ኮሚሽነር ማአ ተሾመ እንደገለጹት የከተማችንን ሰላም አስተማማኝ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ከዚህ ቀደም የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በማበልፀግ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን አሁን ደሞ በከተማው ውስጥ የሚገኙ ሆቴል ቤቶች ያለምንም ድካም ከፖሊስ ጋር በትብብር ለመስራት ያስችላቸው ዘንድ ‹‹ድሬ የተቀናጀ የእንግዶች መረጃ አስተዳደር ሶፍትዌር›› የበለፅገ ሲሆን ይሄን ሶፍት ዌር ወደ ስራ ለማስገባት ይቻል ዘንድ የውይይት መድረኩ መዘጋጀቱን ተናግረዋል፡፡

ከተማችን ድሬዳዋ አሁን ላይ ያላትን ሰላም አስጠብቆ ለማስቀጠል እና የወንጀል መከላከል ስራችንን ስኬታማ ለማድረግ ይሄን የበለጸገ ሶፍትዌር በመጠቀም ሊደርሱ የሚችሉ የወንጀል ተግባራትን ልንከላከል ይገባል ያሉት ም/ኮሚሽነር ማአ ተሾመ በቴክኖሎጂ በመታገዝ የፀጥታን ስራ መስራት የወንጀል ተግባርን ለመከላከል ትልቅ ድርሻ ያለው ሲሆን ይህ የበለፀገው ሶፍትዌር ወንጀለኞችን በቀላሉ ለመያዝና ሽብርተኞችን ወደ ከተማችን ገብተው እኩይ አላማቸውን እንዳያሳኩ ለማድረግ ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ ተገኝተው ስለ ሶፍትዌሩ ገለፃ የሰጡት የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ ጌትነት ቶሎሳ በበኩላቸው ድሬዳዋ ከተማችን የትንሿ ኢትዮጲያ ተምሳሌት በመሆኗ ሰላሟን ለማስፈን በጋራ ጠንክረን ልንሰራ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ይህ ሲስተም ሁለት ጥቅሞች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ለሆቴሎች በየእለቱ በሆቴላቸው የሚያርፉ እንግዶች ለፖሊስ በቴክኖሎጂ በተደገፈ መረጃ ሪፖርት ማቅረብ የሚያስችል ሲሆን ሁለተኛው ጥቅም ደግሞ ፖሊስ ከሆቴል ቤቶች ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ ፈጣን በማድረግ አጠራጣሪ ነገሮች ካሉ በፍጥነት ማጣራት የሚያስችል ሲስተም እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

ሲስተሙን ካበለፀጉት መካከል ዶክተር ጋዲሳ አላኒ አንዱ ሲሆኑ ስለሲስተሙ አጠቃቀም ለሆቴል ቤት ባለቤቶች ገለፃ እና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ከተሳታፊዎችም ለቀረቡ ጥያቄዎች ከመድረኩ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ 105 የሚሆኑ የሆቴል ቤት ባለቤቶች የተሳተፉ ሲሆን ይህ ሲስተም ወደ ስራ ሲገባ እንደ ሀገር አቀፍ የመጀመሪያ ሲሆን ከተማችን ድሬዳዋም የመጀመሪያዋ ተጠቃሚ ትሆናለች ፡፡

## ህጉ ምን ይላል

### የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ክልከላ እና የሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነት

የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ በአንቀፅ 4 የጥላቻ ንግግርን በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት በፅሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪዲዮ ማሰራጨት የተከለከለ መሆኑን ደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ የአዋጁ አንቀፅ 5 የሐሰት መረጃን በአደባባይ ስብሰባዎች፣ በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚዲያዎች ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት በፅሁፍ፣ በምስል፣ በድምፅ ወይም በቪዲዮ ማሰራጨት የተከለከለ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይህንን ክልከላ ተላልፎ መገኘትም የወንጀል ተጠያቂነት የሚስከትል መሆኑን በአዋጁ አንቀፅ 7 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይኸውም፡-

ማንኛውም ሰው የአዋጁን አንቀፅ 4 በመተላለፍ የጥላቻ ንግግር ያደረገ እንደሆነ እስከ 2 አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 100 ሺ ባልበለጠ መቀጮ የሚቀጣ ሲሆን በጥላቻ ንግግሩ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈፀመ እንደሆነ ቅጣቱ ከ1 አመት እስከ 5 አመት የሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል።

ማንም ሰው የአዋጁን አንቀፅ 5 በመተላለፍ ሐሰተኛ መረጃን ያሰራጨ እንደሆነ እስከ 1 አመት የሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 50 ሺ ባልበለጠ መቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል፡፡ በተለይም በሐሰተኛዉ መረጃ ስርጭት ምክንያት ጥቃት የተፈፀመ፣ ሁከት ወይም ግጭት የተከሰተ እንደሆነ ቅጣቱ ከብዶ ከ2 እስከ 5 አመት በሚደርስ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

የጥላቻ ንግግር ወይም የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ወንጀሉ የተፈፀመው ከ5 ሺ በላይ ተከታይ ባለው የማህበራዊ ሚዲያ ገጽ ከሆነ ወይም በብሮድካስት አገልግሎት ወይም በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ውጤት ከሆነ ቅጣቱ እስከ 3 አመት የሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር 100 ሺ ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል፡፡

ሆኖም በጥላቻ ንግግር ወይም በሐሰተኛ መረጃ ወንጀል መፈፀም ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት ያልተፈፀመ ወይም ያልተሞከረ ከሆነ፣ ሁከት ወይም ግጭት ያልተከሰተ እንደሆነ እና ጥፋተኛውን ለማረም የተሻለ ነው ብሎ ሲያምን ፍርድ ቤቱ በእስራት ምትክ የግዴታ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራን በአማራጭ ቅጣትነት ሊወስን እንደሚችል በህጉ ላይ ተደንግጎል።

#### ልዩ ሁኔታዎች

ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ሳይሸራረፍ መከበር ያለበት መብት እንደመሆኑ የጥላቻ ንግግር እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ክልከላ ሀሳብን በነፃ መግለፅ መብት እንዳይጋፋ በጠባቡ የሚተረጎም ነው፡፡



# ስፖርት

19ኛ ዓመት | ቁጥር 859 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ - ጥር / 01 / 2016 ዓ.ም

## "የአንድ ሰዓት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለሚሊዮኖች" ! በድሬዳዋ በድምቀት ተካሄደ

በብሩክ ደስታ

በድሬዳዋ ከተማ አቀፍ የማህበረሰብ ስፖርት "የአንድ ሰዓት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለሚሊዮኖች"! በሚል መሪ ሀሳብ ተካሂዷል።

በድሬዳዋ ምድር ባቡር አደባባይ የህብረተሰብ የአካል ብቃት ስፖርት እንቅስቃሴ ላይ የአስተዳደሩ ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር እና በአለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂው ቲክቶከር ጆሲ ኤንጅል ናርአንዶ ጨምሮ ቁጥራቸው በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች ተገኝተዋል።

ህብረተሰቡ ጤንነቱን እንዲጠብቅ አላማ ያደረገው ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እንደሆነም ኮሚሽነር አቶ ፊራንኦል ቡልቻ ተናግረዋል።

በዝግጅቱ ስፖርት ለሰላምና ለፍቅር ብሎም ለአብሮነት ለማዋል የሰነቀ መሆኑም ተጠቁሟል።

ስፖርታዊ እንቅስቃሴ አዘጋጁ የድሬዳዋ ወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን በብሔራዊ ደረጃ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተካሄደውን የአካል ብቃት ስፖርት እንቅስቃሴ ታሳቢ በማድረግ እንደተዘጋጀም ኮሚሽነሩ ፊራንኦል ገልፀዋል ።



በዕለቱ የድሬዳዋ አስተዳደር ክቡር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር ለታዋቂው ቲክ ቶኮር ጆሲ ኤንጅል ናር ኦንዶ የድሬዳዋን መልካም ገፅታ በቲክቶክ ለመላው አለም በማስተዋወቅ ላደረገው ተግባር የአስተዳደሩ ልዩ የክብር ሽልማት ተበርክቶለታል።

በአለም አቀፍ ታዋቂው ቲክ ቶኮር ጆሲ ኤንጅል ናር ኦንዶ በከተማዋ አስተዳደር እና ህብረተሰቡ ላሳየው ፍቅር አቀባበል እንዲሁም በተደረገለት ስጦታ እጅግ መደሰቱን በመግለጽ አመሠግናለሁ ሲል በመድረኩ ደስታውን ገልጿል።

የአስተዳደሩ ወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ፊራንኦል ቡልቻ ተሳታፊዎች እና ለዝግጅቱ መሳካት አስተዋጽኦ ያደረጉትን አመስግነዋል።

በዚህ ዝግጅት የምስራቅ አየር ምድብ ፣የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አባላት ፣ ስፖርተኞች፣ አሰልጣኞች፣ ዳኞች፣ የስፖርት ባለሞያዎች፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጨምሮ የሴክተር ተቋማት ፣ እና የወረዳ አመራሮችና ነዋሪዎች፣ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ እጅግ በአማረ ሁኔታ ተሳትፈዋል።

**(ምንጭ:ድ/ወ/ስ/ኮ ይፋዊ ገፅ)**

## በኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ ድሬዳዋ እና ፋሲል ከነማ ተገናኝተዋል

በኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ ድሬዳዋ እና ፋሲል ከነማ ሲገናኙ በሊጉ ስምንተኛ ሳምንት ድሬዳዋ ከባህርዳር ጋር ካደረገው ጨዋታ የሁለት ተጫዋቾችን ለውጥ ሲያደርግ ቻርለስ ሙሴጌ እና ዘርዓይ ገብረሥላሴ አርፈው ዳዊት እስጢፋኖስ እና ሙኸዲን ሙሳ መተካት ችሏል።

እጅግ ቀዝቃዛ በነበረው የመጀመሪያ አጋማሽ ሁለቱም ቡድኖች ፈታኝ የማጥቃት እንቅስቃሴ ለማድረግ ሲቸገሩ በኳስ ቁጥጥሩ እና ወደ ተጋጣሚ የግብ ክልል በቁጥር በዝቶ በመድረሱ በኩል ዐፄዎቹ መጠነኛ ብልጫ ነበራቸው።

ወደ ራሳቸው የግብ ክልል ተጠግተው መጫወትን የመረጡት ብርቱካናማዎቹ የተደራጀ የመከላከል ቅንጅት ማሳየት ቢችሉም ከራሳቸው የግብ ክልል በቁጥር በዝተው ለመውጣት ግን ሲቸገሩ ተስተውሏል።

ከዕረፍት መልስ ጨዋታው ተሻሽሎ ሲቀጥል በኳስ ቁጥጥሩ ብልጫ በመውሰድ ተጭነው መጫወታቸውን የቀጠሉት ዐፄዎቹ በተደጋጋሚ ከቆሙ ኳሶች የግብ ዕድሎችን ለመፍጠር ጥረት ማድረግ ችለዋል።

በፋሲል ከነማ የማጥቃት እንቅስቃሴ



ውስጥ ቁልፍ የነበረው ጌታነህ ከበደ ከተደጋጋሚ ጥረቶች በኋላ ያገኘውን የቅጣት ምት ኳስ በአስደናቂ ሁኔታ በመምታት መረቡ ላይ አሳርፎታል።

በተሻለ የራስ መተማመን ላይ በነበሩት ፋሲሎች ተጨማሪ ግብ አስቆጥረዋል። ሽመክት ጉግሳ የሰነጠቀለትን ኳስ ጌታነህ ከበደ በተረጋጋ አጨራረስ ግብ አድርጎታል።

በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎችም ፍጹም ብልጫ በመውሰድ ጨዋታውን ማረጋጋት የቻሉት ፋሲል ከነማዎች በጨዋታው ድንቅ ልዩነት መፍጠር የቻለው ሽመክት ጉግሳ ሰንጥቆ ያቀበለውን ኳስ ተቀይሮ የገባው ናትናኤል ገብረጊዮርጊስ በግሩም አጨራረስ መረቡ ላይ አሳርፎታል። ጨዋታውም በፋሲል ከነማ 3-0 አሸናፊነት ተጠናቋል።

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

## የድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን የ7ተኛ ሳምንት ጨዋታዎች በሳቢያን ሜዳ በድምቀት መከናወናቸውን ቀጥለዋል



የደረጃ ለውጥ የሚያስከትሉ ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን ሀፊተ ኢሳ ድሬ ካባን 3-2 በማሸነፍ ከመሪው መስቀለኛ ጋር ያለውን የነጥብ ልዩነት ማጥበብ ችሏል።

ሳቢያን ህብረት እና ሆርሞድ በርካታ ጎሎችን በማስቆጠር ተጋጣሚዎቻቸውን ማሸነፍ ችለዋል።

መስቀለኛ አዲስ ከተማን እንዲሁም ቀፊራ አሸዋን በተመሳሳይ 1-0 በሆነ ውጤት ማሸነፍ ችለዋል።

06 ህብረት ከገንደ አብዲ ቦሩ, አኳ ድሬ ከ 01 ቀበሌ ጋር 1-1 በሆነ ውጤት ጨዋታቸውን አጠናቀዋል።

የድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን የ8 ተኛ ሳምንት ጨዋታዎች በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት በሳቢያን ሜዳ ይከናወናሉ።